ጳጉሜ-1 ,2012(ወርሀዊ)

ቅንነት ድል ያደርጋል!

# ቅንዴል

ቅፅ-፩ ቁጥር-፩

DIGITAL MAGAZINE



"...ኢትዮጵያዊነት በመወለድና እዚህ በመገኘት የሚሰጥ ዜግነት ሳይሆን ልብ ላይ የሚታነጽ ማንነት ነው።..."

**ዶ/ር ኤሊያስ ገብሩ**

**በብርሀን ዘመን አይኑን የጨፈነ ትውልድ!**

✍ በሀይሉ ወ/ይፍራው

**የአለማችን ድንቃድንቅ ባህሎች**

✍ በነዋል አቡበከር

**ዓይኖችህ ወዴት ያያሉ?**

✍ በቀለዮጳ ደስታ


እንኳን ለአዲሱ ዓመት
በሰላም አደረሳችሁ!
ቅንድል ዲጂታል መፅሔት ለመላው ኢትዮጲያውያን አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የፍቅር፣ የደስታ፣ የመቻቻል እና የአንድነት እንዲሆንልን ይመኛል።
2013 የድል ዓመታችን ነው።
ጥላቻን፣ ቂምን፣ መገፋፋትን፣ መለያየትን በቅንነት እና በይቅርታ ድል አድርገን በአንድነት ወደ ህልማችን ጫፍ የምንሮጥበት ዓመት ነው።እንቁጣጣሽ!
ቅንድል
DIGITAL MAGAZINE

ቅንድል
DIGITAL MAGAZINE

# ማውጫ




**04** ርዕሰ-አንቀፅ

**06** በብርሀን ዘመን አይኑን የጨፈነ ትውልድ
ሀገሬ
በሀይሉ ወንድይፍራው

**09** ምስጢር ነው! ሰው እንዳይሰማ!
አብርሆት
በታምራት ታደሰ

**12** የአውደብሩሀን ገፆች
ቆይታ ከዶ/ር ኤልያስ ገብሩ ጋር

**19** አስገራሚ ባህሎች በዓለም
አጃኢብ
በነዋል አቡበከር

**25** ሰዎች ራሳቸውን ለምን ያጠፋሉ
አዕምሮ ጤና
በፊራኦል መስፍን

**28** ማነው አትችይም ያለሽ?
ንንሳ አወት
በአናናስ ግርማይ

**30** እልፍ ገፆች
በ ዮናስ ሀ/ማርቆስ

**31** አይኖችህ ወዴት ናቸው
ትዝብት
በ ቀለዮጳ ደስታ

**34** ሰርጓጅ መርከቦች ለባዕዳን ውቂያኖስ
ሳይ-ቴክ
በ ለአለም ክንፈ

# ርዕሰ - አንቀፅ

## 'ገበታ ለምክንያታዊ ወጣት ግንባታ' ያስፈልገን ይሆን?

ሀገራችን ኢትዮጲያ የዘመነ መሳፍንቱን ጊዜ ናፋቂ በሚያስብል መልኩ ወጣቶች እና ፖለቲከኞች እንደ ሀገር ከማሰብ ይልቅ ስለ ጎጥ እና መንደሮች ማሰብና መጨነቅ ከጀመርን ቀናት ወራትን፣ ወራት ደግሞ አመታትን እየወለዱ እነሆ ዛሬ ላይ ደርሰናል።
ለዚህም የመንጋነት ደመነፍስን (heredic instnict) ምክንያት ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማሙበታል።
ወጣቶች ከግል እይታ እና ውሳኔ ይልቅ በዘር እና በጎሳ ተቧድነው ፤ ከአመክንዮ ይልቅ በመሰለኝ እና ደሳለኝ ፤ በበሰለ ስሜት ነገርን ከማውጠንጠን ይልቅ በነደደ እና በተቀጣጠለ ስሜት ሆነው የሚወስኗቸው የቡድን ውሳኔዎች የሀገርን ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ህይወት ላይ ትንሽ ነው የማይባል ጠባሳን እየጣለ ይገኛል።
የሀሳብ ልዩነቱን የተገነባውን በማቃጠል እና በማፍረስ የሚገልፅ ኢ-ምክንያታዊ ወጣት ሀገር ለብልፅግና የምታደርገውን ጉዞ ዳገት እንዳያደርግባት የብዙዎች ፍርሀት ነው።
ስለሆነም መንግስት ብልፅግና ያለ ምክንያታዊ ወጣት "ያልተፈታ ህልም" መሆኑን በመገንዘብ በሀገራችን የሚገኙ ወጣቶች ከስሜታዊነት፣ ከቡድንተኝነት፣ ከቂም እና ጥላቻ እንዲሁም ለሰዎች እና ድርጅቶች የግል ፍላጎት መጠቀምያ ከመሆን ይልቅ በምክንያታዊነት ፣ በቅንነት እና በሀገር ፍቅር በማነፅ የሀገራቸው የብልፅግና ጉዞ ላይ ተዋናኝ እንዲሆኑ የሚያስችል የምክንያታዊ ወጣት ማጎልበቻ ፕሮጀክት አስፈላጊ ነው።
በምክንያት የሚያምን ትውልድ/ወጣት የራሱን ሀሳብ በነፃነት የመግለፅ አቅም ያለው እና ከቡድናዊ አስተሳሰብ ተፅዕኖ የተላቀቀ ነው።
ምክንያታዊ ወጣት የሀሳብ ልዩነቱን የተገነባውን በማፍረስ እና በማቃጠል ሳይሆን በውይይትና በሀሳብ ብቻ ይገልፃል። ስለሆነም ምክንያታዊ ወጣት ሀገሪቷ እየሰራች ላለችው ትልልቅ ፕሮጀክቶች ዋስትና ነው።
ለዚህም "ገበታ ለሸገር"......... "ገበታ ለሀገር" ብቻ ሳይሆን ገበታ ለምክንያታዊ ወጣትም ያስፈልገናል።
ገበታ ለሀገር የሚለው ሀሳብ ተፈጥሮ የለገሰችን ሀብቶች ተጨማሪ ዕሴቶችን በመጨመር እና በማልማት የቱሪዝም መዳረሻን መጨመርና የገቢ ምንጭ ለማሳደግ የሚደረግ መልካም ተግባር ቢሆንም ያለ ምክንያታዊ ትውልድ ይህን በአግባቡ መጠቀም እና ማሳደግ ስለማይቻል መንግስት የምክንያታዊ ወጣት ማጎልበቻ በተቋማዊ አደረጃጀት ስር ሊሰራበት ይገባል።

ቅንድል ዲጂታል መፅሔት በቅንድል ኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ማህበር ወጣቶች ተዘጋጅቶ በ E-square አድቨርታይዚንግ እና ኢቨንትስ የሚቀርብ በማህበራዊ፡ ስኑልቦናዊ እና ጤናነክ ጉዳዮች ዙርያ የሚያተኩር ዲጂታል መፅሔት ነው፡፡
የካቲት 2011 ተቋቋመ፡፡

✔ አድራሻ
✆(+251)912178520
✆(+251)920019699
e-mail- kdigitalmagazine@gmail.com



### አዘጋጅ

በሀይሉው/ይፍራው ( መባ)
e-mail- ethiomebreku3000@gmail.com
Telegram-@Dasolo
✆(+251)924140293



### አዘጋጅ

ነዋልአቡበከር
e-mail-newalabubeker13@gmail.com
Telegram-@entisar13
✆(+251)937683378



### ም/አዘጋጅ

ነፃነት ጌታቸው
netsanetg43@gmail.coment
Telegram-@mistretigist
✆(+251)953498678



### ማኔጂንግ ዳይሬክተር

ኤርሚያስ ደጀኔ
e-mail-ermiyasdejene@gmail.com
Telegram-@jeremy00
✆(+251)912178520



### አርታኢ

አወት ሀይለስላሴ
e-mail-awoth12@gmail.com
Telegram-@Awicha12
✆(+251)920152581

### የመፅሔት ዲዛይን

MHgraphics
e-mail-EsruMH1@gmail.com
Telegram-@MHgraphics
✆(+251)920019699



### አርት ዳይሬክተር

ፍራኦል መስፍን
firaolmesfin8@gmail.com
Telegram-@forgiven247
✆(+251)923602445



### አርታኢ

ቀለዮጳ ደስታ
e-mail-cleopadada2012@gmail.com
Telegram-@adadada8
✆(+251)941535884



### ማርኬቲንግ

ዮናስ ኃ/ማርቆስ
e-mail-lijyoha2@gmail.com
Telegram-@Yonas_H
✆(+251)970514616



### ማርኬቲንግ

ያሬድ ለማ
e-mail-Yaredlemma487@gmail.com
Telegram-@Yared4444
✆(+251)932540523

ቅንነት ድል ያደርጋል!



በሀይሉ ወንድይፍራው(መባ)
በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ የማኔጅመንት
መምህር እና ቢዝነስ ሪሰርቸር
ethiomebreku3000@gmail.com





# በብርሀን ዘመን አይኑን የጨፈነ ትውልድ!

የሰው ልጅን ጠልተን - ከወደድን መሬቱን
እኔነት አንግሰን - ከተውን እኛነቱን
በስሜት ተሞልተን - ከካድን እውነቱን
አመክንዩ አልባዎች - ሀሰት ከሰበኩን
ያው ፍጻሜው ቀርቧል- ሰይጣን ሊያስመልኩን፡፡

ሁላችንም ተመሳሳይ እንደሆንን አምናለሁ፡፡ ተመሳሳይ ስል የሀሳቦችን መመሳሰል ወይም ሌሎች የባህሪያትን ጥርቅም ማለቴ አይደለም፡፡ በርግጥ ሁላችንም ሰዎች ነን ፣ ሁላችንም ሰብዓዊ ፍጡራን ነን፡፡ ምን አልባት በየአካባቢያችን ያለው ባህል እና አኗኗር ይለያይ ይሆናል፡፡ ምን አልባት በእምነት፣ በጎሳ፣ በቋንቋ እንለያይ ይሆናል፡፡ ሆኖም ሁላችንም ሰብዓዊ አካልና አዕምሮ ያለን ሰብዓዊ ፍጡራን ነን ፤ በተመሳሳይ መልኩ እንደተወለድን በተመሳሳይ መልኩ እንሞታለን፤ የሰውነት ቅርጻችን፣ የአዕምሮ አሰራራችንና ስሜታዊ አፈጣጠራችን ተመሳሳይ ነው፡፡ በምድር ላይ ያለን ሁላችንም የሰው ልጆች የሚያገናኘን ይህ የሰብዓዊነት ጥግ ነው፡፡ ነገር ግን በተለየ ሁኔታ ደግሞ በአንድ የጂኦግራፊካል ቦታ መገኘት፣ ተመሳሳይ ባህል ፣ ተቀራራቢ ታሪክ ሲኖር ደግሞ ከሰብዓዊነት በበለጠ ብዙ የሚያቀራርብና የሚያገናኝ ማኅበረሰብ ይፈጠራል፡፡ እኛም ኢትዮጲያውያን ሰብዓዊ ተፈጥሯችን ከሌላው ዓለም የሰው ልጆች ጋር ሁሉ ሲያመሳስለን ከፍ ባለ ደረጃ ደግሞ ባህላችን፣ አኗኗራችን፣ የማኅበረሰባችን ስነ-ልቦና፣ ታሪካችን እና ሌሎች የማኅበረሰብ መገለጫዎች በእጅጉ የሚያቀራርበን የአንድ ሀገር ህዝቦች እንደሆንን መስካሪ አያሻውም ፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ አንድነት ከሚታየውና ከሚነገረው ልዩነት የበለጠ መሆኑን የሚክድ ትውልድ ካለ እራሱንና ታሪኩን መፈተሽ አለበት ብዬ አምናለሁ፡፡

ሰላም ሰላም ውድ የሀገሬ አምድ አንባቢያን እና የቅንድል ቤተሰቦች እንደምን ቆያችሁ? ሳምንታቶቹ ለአንዳንዶች የተስፋ፣ ለአንዳንዶች የስጋት ከመሆን በዘለለ የብርሃን ምልክትም ያየንባቸው እንደሆኑ ተስፋ አድርጋለሁ፡፡ ታዲያ በዛሬው የሀገሬ አምድ በሀገራችን ኢትዮጲያ በተለያዩ ግዜያት በአንዳንዶች ተወቃሽ በራሱ ደግሞ ከሳሽ እየሆነ ያለውን ወጣት ትውልድ ከሀገራዊ ትዝብቶች ጋር ለመቃኘት ወደድኩ፡፡

ኢትዮጲያ በትውልድም ሆነ በታሪክ ከዓለም የከፍታ ማማ ያስቀመጡ ታላላቆችን ከማፍራት ጀምሮ በርካታ ገድል የፈጸሙና እየፈጸሙ ያሉ ወጣቶች እንዳሉ የሚክድ የለም፡፡ ነገር ግን በዛው ልክ በተለይም አሁን ባለንበት ዘመን እውነትን የሚመረምር፣ ጠያቂ፣ በእውቀት የሚመራ፣ ከእኔነት እኛነትን የሚያስቀድም፣ ከስሜት ምክንያትን መለያው የሚያደርግ ወጣት ተመናምኗል ብል ማጋነን አይሆንብኝም፡፡ ምክንያቱም አሁን ላይ የወጣቶች መለያ እየሆነ የመጣው የጥላቻ መሳሪያ መሆን፣ በተቀደደለት ቦይ እንደሚፈስ ውኃ በተሰመረልን ብቻ እየኖርን ከሰፊው ሰዋዊነት ይልቅ ማንነትን በሚያናጋ ተግዳሮት ውስጥ እንገኛለን፡፡ ከወራቶች በፊት በሀገራችን የተከሰቱትን ክስተቶች አንስቼ ልጠይቅ ወይም ልታዘብ ሳይሆን በቅርብ ዓመታት ውስጥ የዚህ ትውልድ መለያ ተደርጎ ስለሚወሰደው ስሜታዊነት፣ አላዋቂነት፣ ባዕድ አምላኪነት፣ ግዴለሽነትና ምን አገባኝ ለሚሉ የዘመን ጭለማዎቻችን ብርሃን የሚሆኑ ሀሳቦችን ለማንሳትና ችግሮችን ልሞግት ነው የምፈልገው፡፡

ሀገራችን የብዙኃን ጥቂቶች ስሜት መግለጫ ሆናለች፣ ጥቂት ተምረው ብዙ ያላወቁ፣ ጥቂት የተመራመሩ፣ ጥቂት የታገሉ፣ ጥቂት ያታገሉ ብቻ የሚዘውሯት ብዙኃንን ታዛቢ አድርጋ የጫነች በቅሎ ሆናለች። ትውልዱ መቼ እንደሆነ ባላቅም  ስሜት የሚመራው ግዴለሽ ሆኗል ፣ ለጥቂት ሰዎች ሙቀት ሲል እንደ እሳት የሚነድ ማገዶ የሚሆን ወጣት በዝቷል፣ ለምን? ብሎ መጠየቅ ነውር የሚመስለው ብዙ ነው። ብዙዎች ስላረጉት ብቻ ሀሰትን የምንቀበል ሆነናል። የሰዎች ሰቆቃ መስማት ተስኖናል፤ ችግራችንን ለመለወጥ ሳይሆን ችግራችን ላይ መከራ ለመደመር እየተጣደፍን ነው። ከወገኖቻችን ራብ ይልቅ የፌስቡክ አርበኛ ቀልባችንን ይገዛናል። ከእውቀት በላይ ወረቀት ብቻ መሰብሰብ መለያ ሆኗል፤ ስለ ዓለም እየተማርን ስለ ራሳችን ቤት መጨነቅ እንኳን አልቻልንም። በብርሃን ዘመን ዓይናችንን ጨፍነን መራመድ መርጠናል። በምግብ እጦት እልፎች እየረገፉ ለልደት ውስኪ የሚራጩ፣ ለጭፈራ የተገዙ ዘመነኞች መሆንን መርጠናል። ወጣቶች እየሞቱ ዛሬም ለራሳችን ምቾት ብቻ የምንጨነቅ መሆንን እንዴት ቻልን? በእኔ እምነት ወይ ተስፋ ቆርጠናል ወይ ግዴለሽ ሆነናል። ስሜት ለጥፋት የሚዳርግ ግልብ የሆነ መሪ ነው። ይህ ጊዜ ህይወት አስይዘን የምንጫወትበት አባሮሽ ሳይሆን እንደ ግለሰብ፣ እንደ ማኅበረሰብ፣ እንደ ተቋም ሁሉም ቆም ብሎ የሚያስብበት ነው።

ይህ ትዝብቴ እንጂ ወቀሳ አይደለም እኔም የዚህ ዘመን ወጣትና ትውልድ ነኝ ግን የማምንበትን ነገር ለመቀበል ለምን ብሎ የሚጠይቅ ነጻ ፍቃድ ያለኝ የሰው ልጅ ነኝ። ሁሉም የዘመኔ ወጣት እራሱን የሚመራበት ነጻ ፍቃድ አለው። ሌሎች የሰሩት ሮቦት ወይም አሻንጉሊት አይደለም ለሌሎች ህልም የራሱንና የሀገሩን ህልም የሚቀብር። የሚገርመኝ በሀገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ትምህርት ቤቶች እየበዙ የተማረ የሚባለውም ቁጥር እየጨመረ ነው። ነገር ግን የተማርነው ምንድነው? ስል መልስ አጣለሁ።

ምክንያቱም የመማር፣ በሀይማኖት የመኖር ትርጉሙ መመርመር፣ ማወቅ ፣ መጠየቅ፤ ክፋት ፣ ጥላቻን መጠየፍ እና ሰውን መውደድ ነው። ሰው ከተማረ እንደ መንጋ አይነዳም፣ እንደ ልጅ አይታለልም፣ የሚያምነውን ወይም የሚያምንበትን ለምን? ብሎ ይጠይቃል፤ እንዴት? እያለ ይፈትሻል። የተሸከመውን የጨለማ፣ የፍርሃትና የድንቁርና ቆፈን እያራገፈ ወደ ብርሃን ይጓዛል።  የዘመኔ ወጣት የሀገሩን ታሪክ፣ ነጻነት፣ እምነት፣ ባህል፣ አብሮነት፣ እውቀትና ጥበብን እንደ የመገናኛ ብዙኃን ብዛት፣ የስልክ አፕሊኬሽን ቢያውቅ እመነኝ የከበበውን ስሜታዊነት ድል ለማድረግ ጥሩ ስንቅ ያገኛል። የሚጠይቅ ያውቃል፤ የሚያውቅ ደግሞ የመፍትሄ እንጂ የችግር አካል አይሆንም። ወጣቱ ላይ ተጣብቆ ተወቃሽ ለማድረግ የሚሞክር ግለሰብ ሁሉ ሊያውቀው የሚገባ ነገር ቢኖር ይህ ሁሉ ችግር የተፈጠረው በዘራው የክፋት፣ የጥላቻ ዘር እንጂ ተፈጥሮ የሰጠችው ተክል ሆኖ አይደለም። እያንዳንዱ የብርሃን ችቦ የሚበራው ከግለሰቦች የልብ ቅንነት፣ ምክንያታዊነትና ሀገር ፍቅር ነውና ሀገሩን የሚወድ ትውልድ ልቡን በቅንነት አዕምሮውን በእውቀት እጆቹን በጥበብ ይቃኝ። ስጀምር እንዳስቀመጥኩት ሁላችንም ሰብዓዊ ፍጡራን ነን። በክልልና በብሄር አጥር ለሚያጥሩን ልንነግረው የሚገባ ሀቅ ይህ ነው። መጀመሪያ ሰውነትን እንቀበል፤ የሰውን ልጅ ሁሉ እንውደድ። ሲቀጥል የማንነታችን ክታብ ሀገር ነውና ሀገራችንን እንውደድ፤ ሀገር ማለት ደግሞ በእያንዳንዳችን ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነትና ልማድ ከ80 በላይ በሆኑ ውብ ሰበዞች የተሰፋች የሁላችን መሶብ ነች።

ወጣትነት በማስተዋል ብርሀን የምንሞላበት የህይወት ምዕራፍ ነው። ወጣትነነት ለአላማ መኖር ነው። ወጣትነት ችግርን መፍጠር ሳይሆን ችግር መፍታት ነው። ወጣትነት ፍቅርና አንድነትን መስበክ ነው። ወጣትነት እራስን በዝሙት ባህር አስምጦ፣ እራስን በመጠጥ ጠርሙስ ደብቆ ፣ በሺሻና በሲጋራ ጭስ  ውስጥን ኩሽና ማድረግ ሳይሆን ስሜት የመግዛት ጥበብ ነው። ወጣትነት ብርሃን ነው። ወጣትነት በቀናነት ብርሃን ልቦናን ሞልቶ ህልምን ለማሳካት የምንፍጨረጨርበት የከፍታ ዘመን ነው።

ስለዚህ የኔ ዘመን ትውልድ ‘ለሀገሬ ምን ልስራላት?’ በሚል የከፍታ ሀሳብ ከፍ ብሎ ስለ ሰውኛነት የሚያቀነቅን እንደሚሆን እምነት አለኝ ። ለዚህም በሁሉም የሀገራችን ክፍል የምትገኙ ወጣቶች ከሚያጠፋፋ ጥላቻ፣ ከሚከፋፍል ክፋት፣ ከስሜታዊነት፣ ከግለኝነት ወጥተን ለዘመን የሚተርፍ የእድሜ፣ የሀሳብ፣ የጤና ባህል ጸጋ ተሰጥቶናልና  እንጠቀምበት። በስሜት ያፈረስነውን በምክንያታዊነት እንገንባው። በሀሰት የሰበኩንን በእውነት እናሸንፋቸው፤ በጥላቻ የጻፍነውን ክፋት በይቅርታ እንፋቀው። ይህ ነው የተሻጋሪ ትውልድ መለያ በምክንያታዊነት፣ በቅንነትና በሀገር ፍቅር የሚራመድ ትውልድ የጎበጠን ያቀናል፣ የፈረሰን ይገነባል ። ከዚህ በኋላ ለአንድነትና ለእድገት እየሰራ የሚሞት እንጂ ለጥፋትና ለልዩነት የሚሞት ትውልድ መኖር የለበትም… ይህ መቀበል ያለብን ሀቅ ነው።

ስሜት፣ ጥላቻ፣ ክፋት፣ መለያየት፣ ዘረኝነትና አለማወቅን ጥለን በእውነትና እውቀት ደምቀን አለማቀፋዊ አስተሳሰብ ባለቤት በመሆን ከትናንት ታሪክ ተምረን፣ ዛሬን ተመራምረን፣ ነገን አሻግረን የምናይ ከተጣላንባቸው ይልቅ በመዋደድና በአንድነት የኖርንባቸውን ውብ ባህሎች በመያዝ በእያንዳንዱ ቀን ጉዟችን ለሀገራችን ከፍታ፣ ለህዝባችን አለኝታ፣ በመጪው ትውልድ ተመስጋኝ በመሆን የሚወቀስ ሳይሆን የሚወደድ ትውልድ ሆነን ኢትዮጲያዊነትን ከፍ አድርገን የያዝን እንድንሆን ለዘመኔ ትውልድ ጥሪዬን እያቀረብኩ የዚህ ዕትም የሀገሬ አምድ ጽሁፌን አበቃሁ። በቀጣይ በሌላ ርዕስ እስከምንገናኝ በቅንነት፣ በመልካምነት እና በሀገር ፍቅር እያንዳንዱን ቀን እንድታሳልፉ እየተመኘሁ በበረከት በላይነህ ግጥም ተሰናበትኩ።

**ይነጋል**

ታድለሻል ቢሉም፣
የ13 ወር ፀሀይ፣ የ13 ወር ፀጋ
ብርሃንሽ ተሰርቆ፣
ሲጨላልም እንጂ፣ መች አየን ሲነጋ?
ተፈጥሮ ቸር ሆና፣
ሰማይዋ ባይነጥፍ፣ ምድሯ ቢለመልም፣
ከልጆቿ ልብ ውስጥ፣
ፍቅር ሲጎድል ነው፣ ሀገር የምትጨልም!፣
"አረ ነግቷል" ቢሉ የታለ የነጋው?
አዕላፋት ተቧድነው፣ በየጎጥ በመንጋው፣
ሰው ከነገ ይልቅ፣ ዛሬን እያሰጋው… የታለ የነጋው?
ታሪኩን እንዳይፅፍ፣ ትውልድ እጁ ታስሮ፣
በትላንቱ ሾተል ዛሬው ተሸንቁሮ፣
ባልኖረው ተካሶ፣ ባልሰራው ተዋቅሶ፣
ለፀብ መዶለቻ፣ ያ'ያቱን ስም ጠቅሶ፣
ላለፈው ሲናከስ ለመጪው ሳይተጋ፣
በምን ስሌት ይሆን፣
ትዉልዷ ጨልሞ ሀገር የምትነጋ?
የህሊና መስታወት በጥበብ ሲፀዳ፣
ማስተዋል እንዳ'ደይ፥ ፈክቶ ሲፈነዳ፣
መገፋፋት ሲቀር ፥ መደጋገፍ ነግሶ
አንዱ ማገር ሲሆን፣ ሌላኛው ምሰሶ፣
የአብሮነትን ሸማ፥ ትዉልዱ ሲሸምን፣
ያኔ ነው ሀገሬ፥ መንጋቷን የማምን።

ሀገሩን የሚወድ ትውልድ ልቡን በቅንነት፣ አዕምሮውን በእውቀት፣ እጆቹን በጥበብ ይቃኝ!

ኢትዮጲያ ለዘላለም በህዝቦቿ ፍቅር ትኑር…





**ታምራት ታደሰ ደነቀ**
የትምህርት ጥራት አማካሪና አሰልጣኝ
email:-Addisayer@gmail.com



# ምስጢር ነው ሰው እንዳይሰማ!

"ሁሉም ነገር ድብቅ በሆነበት ባህልና ሥርዓት ዉስጥ
ሃገር በክብር ህዝብም በህሊናዉ
ያድጋል ብሎ መገመት የማይታሰብ ነዉ።"

ምስጢር ማለት ምን ማለት ነዉ? ምስጢር ማለት ጉዳዩን ካሰበዉና ከጠነሰሰዉ ሰዉ በስተቀር ማንም የማያዉቀዉ ማለት ሲሆን ሌላዉ ትርጉም ደግሞ ማንም ሰዉ እንዳያዉቀዉ የተደረገ፤ የሃገርን ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችልና ያለ ልዩ ፍቃድ ለህዝብ እንዲደርስ የማይፈቀድ፤ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ሊያዉቁት የሚገባዉ መረጃ፤ ወይም ደግሞ በግላችን ልንደርስበት ያቀደነዉን የግል ዓላማ እንደምስጢር ልንይዘዉና ለማንም ልናካፍል የማንገደደዉ ጉዳይ ማለት ነዉ።
የምስጢር ዋጋዉ ብዙ ነዉ። ለዚህም ነዉ ሃገራት የራሳቸዉን የሥለላ ሠራተኞችን በመቅጠርና በማሰልጠን ወደ ተለያዩ ሃገራት በመላክ የሃገራትን ምስጢር እንዲያቀብሏቸዉ የሚያሰማሩት። የሥለላዉ መረብም ከሰፈር ከጎጥ ከቀበሌ እስከ ሃገር ከዚያም አልፎ አለም አቀፍ ይዘት ሲኖረዉ ሃገራት ደግሞ የራሳቸዉ ምስጢር እንዳይወጣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ ለዚህም ነዉ ምስጢር ሚስጥርነቱ ተጠብቆ እንዲቆይ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርጉት። በብዙ ሃገሮች ህግ በማዉጣት ምስጢር የጊዜ ገደብ ኖሮት ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የመንግሥት ምስጢር ለህዝብ ይፋ ይደረጋል። ለምሳሌ በዩናይትድ ኪንግደም በምስጢር የተያዙ የመንግስት ሰነዶች እስከ 30 ዓመት በምስጢርነት ይያዙና ከዚያ በኋላ ለህዝብ ይፋ ይደረጋሉ ሆኖም ግን ሁሉም ሳይሆን ወደ ህዝብ ቢደርሱ ጉዳት የማያደርሱ ስለመሆናቸዉ ሲረጋገጥ ብቻ ነዉ። አለበለዚያ ግን የሰነዱ ምስጢርነት ከፍተኛ ከሆነ 40 ወይም 75 ከዚያም አልፎ 100 ዓመት ከህዝብ ተደብቆ ሊቀመጥ ይችላል።

በሃገራችንም ምስጢራዊ ለሆኑ ጉዳዮችና ለህዝብ ይፋ የሚደረግበት ጊዜ በህግ ስለመደንገጉ የማዉቀዉ ጉዳይ ባይኖርም የተለያዩ ምስጢራዊ ሰነዶች ደረጃ ወጥቶላቸዉና ለምሳሌ "ብርቱ ምስጢር"፤ "ምስጢር"፤ "ጥብቅ" ና "ክልክል" በመባል በማህተም ተረጋግጠዉ ደረጃ ወጥቶላቸዉ በመዝገብ ቤት ዉስጥ በጥንቃቄ ይቀመጣሉ። ሆኖም ግን መንግሥት ቶሎ ቶሎ በሚለዋወጥበት ብዝሃነት በሚስተናገደበትና የብቃት ችግሮችና የተለያዩ ፍላጎቶች ባሉበት ሁኔታ ብዙዉን ጊዜ ምስጢር በቀላሉ እየወጣ ወደ ህዝብ ጆሮ ይደርሳል። የምስጢር በቀላሉ ወደ ህዝብ ጆሮ መድረሱ ደግሞ ሊያመጣ የሚችለዉ ጉዳት ወይም ኪሳራ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ የሚያስከፍለዉ ዋጋ በገንዘብ ሊገመት አይችልም።
በዚህ ርዕስ ላይ ለመፃፍ ያነሳሳኝ የራሴን የህይወት ተሞክሮና በተለያዬ አጋጣሚ የሰማኋቸዉ ምስጢሮች ሁሉ ምስጢር እንዳልሆኑ፤ ቢሆኑ እንኳ ትልቅ ጥንቃቀቄና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸዉ ስለመሆኑ ለመግለፅ ስል ነዉ። ብዙዉን ሞይወትዉበትናጊዜ ማንም እንዳይሰማ በምስጢር ያዢዉ፣ ያዘዉ፣ ያዙት እየተባለ በየሠፈሩ ስንቱ ምስጢሩን አባከነ ህሊናዉንስ ጎዳ፣ ፈጣሪዉንስ አሳዘነ፣ በስህተቱስ ስንቱ ተቀጣ፣ ተዋረደስ፣ ተናቀስ፣ በፍርድስ ተንገላታ።

ምስጢር ምስጢር የሚሆነዉ በጥንቃቄ ሲያዝና አንድ ወይም የተወሰኑ ሰዎች ወይም ቡድን ብቻ ሲያዉቀዉና ደንብና ሥርዓት ኖሮት በህግ የተደነገገ መመሪያ ሲወጣለት፣ ተጠያቂነትም ሲኖረዉ ወይም በሰዎች የህሊና ዳኝነት ከፍተኛ ጥበቃ ሲደረግለት ምስጢር ይሆናል። ምክንያቱም መንግሥት ሲቀየር ወይም ሰዎች ሁለትና ከዚያም በላይ ሆነዉ በስምምነት በፍቅር በነበሩበት ወቅት ያደረጉት ምስጢር እነዚሁ ሰዎች ወይም ቡድኖች በተጣሉ ወይም በተፋለሱ ጊዜ በምስጢር የያዙት ጉዳይ ብዘዉን ጊዜ ለህዝብ ይገለጣል ያንንም ተከትሎ ሰዎች ለከፍተኛ ፀብና ችግር ይጋለጣሉ።

ስለዚህ ምስጢር ጥበቃ ከሌለዉ ምስጥ እንደበላዉ እንጨት መሆንና በቀላሉ ለጠላት ወይም ለተቀናቃኝ ጥቃት መጋለጥ ይመጣል። አበዉ እንደሚሉት “ጠላት ከሩቅ አይመጣም” ። አብዛኛዉ ጊዜ የሚያጠቃን ምስጢራችንን በቅርብ የሚያዉቅ ሰዉ ነዉ። መንግሥትም የራሱን ምስጢር በጥንቃቄ ካልያዘ በተቀናቃኝ ወይም ተፎካካሪ ፓርቲ በዉድድር ሊሸነፍና መራጭ አጥቶ ከሥልጣን በቅሌት ሊባረር ይችላል።

ምስጢር በመያዝ የራሴም ልምድ እንዲህ ነበር። ልጅ ሆኜ በትምህርት ቤት፣ በሰፈር ጓደኞቼ እንዲሁም በዘመዶቼና በወላጆቼም ፊት ይህንን ምስጢር ለማንም እንዳትናገር የተባልኩበት አጋጣሚዎች በጣም በዙ ናቸዉ። አሁን ግን ህሊናዬ ዳብሮ እራሴን አወቄ የፈጣሪን ጥበብና ትልቅነት ስረዳ ያ በልጅነቴና በጨቅላ ዕድሜዬ ያጋጣሙኝና የተነገሩኝ ምስጢር የተባሉ ነገሮች ሁሉ ከንቱና ዋጋ የሌላቸዉ፣ ሁሉም ነገር በፈጣሪ ፊት ግልፅ የሆኑ መሆኑን ሳስበዉ ለካስ ለማንም እንዳትናገር ብለዉ ያሉኝ ሰዎች ህሊናቸዉ ያልዳበረ ወይም ያላደገ እራሴንም ጨምሮ የሰዎችን ጥፋትና መጥፎ ደርጊት እያየን አጥፊዎችን ሳንወቅስ፣ ተጠያቂም ሳናደርግ እየቀረን እዉነትን አቀጭጨን፣ በሰዉ ልጅ ላይ የሚደረጉ መጥፎ ሥራና ጥቃቶችን ሁሉ ምስጢር እያልን፣ እያዬን እንዳላዬ ሆነን መኖር ባህላችን ሆኗል። ይህ ባህሪ ደግሞ ሰዉን ከእንስሳ የሚያቀራርበዉ በመሆኑ ህሊናችን እንዳላደገና እኔም የችግሩ ሰለባ ሆኜ ማደጌን ስረዳ በጣም ይገርመኛል።

ዛሬም ቢሆን በግለሰብም ይሁን በየቢሮዉ በፖለቲካ ሥርዓት ዉስጥ ያሉ፣ በቤተሰብ በጓደኛሞች መሃል ሁሉም የየራሳቸዉ የሆነ ምስጠር አላቸዉ። ከዚያም አልፎ በትዳር ዉስጥ ሆነዉ ሰዉ አዩኝ አላዩኝ እያሉ የሚማግጡ፣ ሌላ ሰዉ እንዳይሰማ ወይም ለሰዉ ይናገርብኝ ይሆን ወይም ትናገርብኝ ይሆን እያሉ በአደባባይ ከሚስጥረኞቻቸዉ ጋር በተያዩ ቁጥር በድንጋጤ ተሳቀዉ የሚኖሩ ሰዎቸም አጋጥመዉኛል። ሀሊናቸዉን ሸጠዉ ዕዉነትን ክደዉ ከሴይጣን ጋር ህብረት ኖሯቸዉ በምስጢር ወንድም ወንደሙን፣ ባለትዳር የትዳር ጓደኛዉን እያታለለ አሳዛኝና ልብን የሚሰብር ሥራን የሚሰራ ግን በፈጣሪ ፊት ሥራዉ የተገለጠ መሆኑን መፅሐፍ ቅዱስ አንብቤ ሥረዳ ድንጋጤዬ በህይወቴ ሙሉ የማልረሳዉ አጋጣሚ ሆኖልኛል። በመፅሐፍ ቅዱስ ትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 23፡ ከቁጥር 23 – 24 እንዲህ ይላል። “እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰዉ በስዉር ቢሸሸግ እኔ አላየዉምን? ሰማይንና ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? በተጨማሪ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 12፡ ከቁጥር 2 – 3 “ነገር ግን የማይገለጥ የተከደነ፣ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም። ስለዚህ በጨለማ የምትናገሩት ሁሉ በብርሃን ይሰማል፣ በእልፍኝም ዉስጥ በጆሮ የምትንሾካሾኩት በሰገነት ላይ ይሰበካል”። ይልና ምንም ዓይነት ምስጢር በፈጣሪያችን ፊት የተሰወረ አለመሆኑን በቃሉ አረጋግጦልናል።

ሰዉ ከእንሰሳት የሚለይበትና የሚሻልበት ዋናዉ ነገር የሚያስብና የሚያመዛዝን እራሱን የሚገዛበት ኣእምሮ ስላለዉ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ዉሳኔዉን የሚመዝንበት፣ የፈጣሪዉን ባህሪ የመሰለ በየዕለቱ ሊያሳድገዉ የሚችለዉ የዕዉነት መንፈስ ወይም ህሊና ያለዉ በመሆኑ ነዉ። ስለዚህ ሰዉ ከእንሰሳ በላቀ ደረጃ ማሰብ የሚችልና ጥሩና መጥፎዉን መለየት የሚያስችል አቅም ያለዉ ፍጡር ነዉ። ነገር ግን ፈጣሪ ለሰዉ ልጅ የሚጠቅምን ህግ አዘጋጅቶ በሙሴ በኩል ለህዝቡ ቢሰጥም የሰዉ ልጅ ብዙ ባወቀበትና በተመራመረበት በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ተደብቆ የሚሰራዉ ተንኮል፣ ሸር፣ ሐጢያት ከመብዛቱ የተነሳ በራሱ ላይና ለትዉልድ በሚያልፍ ማብቂያ በሌለው የህይወት ዉጣ ዉረድ ዉስጥ እራሱን ያገኛል።

ሰዉ ሆኖ የማይሳሳት የለም ነገር ግን ሰዉ በስህተቱ ተፀፀቶ ንስሓ ካልገባ፣ በዳይ ተበዳይን ይቅርታ ካልጠየቀ፣ ዓይንን በጨዉ ታጥቦ "ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል" እንደሚባለዉ አጥፊዎች ሓጢያታቸዉ በዝቶ የሁሉም ስህተት በምስጢር ተይዞ ከቀረ የአንዱ ስህተት ለሌላዉ ትምህርት የሚሆንበት መንገድ ስለሌለ ሁሉም ተያይዞ ቁልቁል ወደ ገደል መዉረድ ይሆናል። እዚህ ለይ ግን በፍርድ እጦት ምክንያት ሰዉ በምድር ላይ በሠራዉ ሥራ ተጠያቂ ካልሆነ ተበዳይ ቢጎዳም የሚበቀል አምላክ ስላለን ንፁሐን ተስፋ ሳይቆርጡ ሊፅናኑ ይገባል። ይህንንም በመፀሐፍ ቅዱስ መክብብ ምዕራፍ 12፡ ከቁጥር 13 – 14 "እነሆ የነገሩን ሁሉ ፍፃሜ እንስማ ፤ እግዚአብሔርን ፍራ፣ ትእዛዛቱንም ጠብቅ፣ ይህ የሰዉ ሁለንተናዊ ተግባሩ ነዉና። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረዉንም ነገር ሁሉ ፡ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ፤ አንድም ሳይቀር ማንኛዉንም ወደ ፍርድ ያመጣዋልና" ይላል።

ይህን የመሰለ የፈጣሪ ቃል መኖሩ ደግሞ የክፋት ምስጢርን በሚያደርጉ ንፁሃን ቢጎዱም ዕዉነተኛ ፈራጅ ስላለ መፅናናት ይገባናል፣ በቃሉም ልንበረታ እንችላለን። ይህ የመጨረሻዉ የፍርድ ደረጃ ሲሆን ከዚያ በፊት ግን ማድረግ ያለብን ምንድነዉ ብለን እራሳችንን ብንጠይቅ መልሱ ይህ ነዉ። የአንድ ሰዉ የሕይወት ልምድ ለሌላዉ ትምህርት ካልሆነ፣ ሥህተታችንን እየደገምን ባለንበት መርገጥና አለማደግ ከሆነ፣ ችግሩ ከፍተኛ የሆነዉን የባህል ተፅእኖ ማለትም የሚረባዉንም የማይረባዉንም ምስጢር ከሚባልበት አዙሪት ሰብረን መዉጣት እቅቶን ተስማምተን እየኖርን፣ ሰዉን የሚያዋርደዉንም፣ የሚያስፈርጀዉንም፣ በፈጣሪ ፊትም ነፍሱን የሚያሳጣዉንም ሳንለይና ሁሉንም ምስጢር ነዉ ሰዉ እንዳይሰማ አፍነን ከያዝን፣ ሰዉ ከስህተቱ እንዳይማርና ከዓመት ዓመት አንድ ዓይነት ነገር እያደረገ፣ ዘንድሮ ይሻላል ስንል እየባሰ ከመጣ እኛዉ የችግሩ መንስኤዎች መሆናችንን ማወቅና ማመን አለብን። እርግጠኛ ለመሆንም እራሳችንና ባህላችንን ፈትሸን መለወጥ ያለብንን መለወጥ፣ መሻሻል ያለበትን ማሻሻል፣ መቅረት ያለበትን ማስቀረት አለብን። በሌለ በኩል ደግሞ የአንዱ ስህተት ለሌላዉ ትምህርት መሆን ሲገባዉ መሳቂያና መሳለቂያ ካደረግነዉ ማንም ስህተቱንም ሆነ ምስጢሩን በግልፅ ለመናገር አይደፍርም። በመጨረሻም ትንሹም ትልቁም ጉዳይ ድብቅና ምሰጢር በሆነበት ባህልና ሥርዓት ዉስጥ፣ የፈጣሪንም ሃይል፣ ጥበብ፣ ዕዉነተኛ ፈራጅነት፣ በሁሉም ሥፍራ በአንድ ገዜ መገኘት መቻሉን የመረዳት አቅሙ ከሌለ ሃገር በክብር ህዝብም በህሊናዉ ያድጋል ብሎ ማሰብ በህልም እንጀራ መበላት ነዉ።



ሰላም ውድ የአውደ - ብሩኃን ገፆች አንባቢያን እንደምን ቆያችሁን? እንደሚታወቀው የአውደ - ብሩኃን ገፆች አምድ ላይ በሀገራችን በተለያዩ የሙያ መስክ ተሰማርተው ለሀገራቸው መልካም የሚባሉ ትሩፋቶችን ያበረከቱ ግለሰቦች እና በመዝናኛው ዘርፍ፣ በትምህርት፣ በቢዝነስ፣ በስፖርት፣ በኪነ-ጥበብ እና በሌሎች መስኮች በሰሯቸው ተግባራት ለወጣቶች አርአያ የሚሆኑ እና አንባቢያንን እያዝናኑ የህይወት ስንቅ ያስይዛሉ ያልናቸውን እንግዶች የምናቀርብበት መድረክ ነው፡፡

የዛሬው የአውደ - ብሩኃን ገፆች እንግዳችን ባለ ዘርፈ ብዙ ሙያ ባለቤት የሆነው ዶ/ር ኤሊያስ ገብሩ ሲሆን ብዙዎቻችን ‘ኤትዮጵ’ በሚለው ተወዳጅ ልቦለዱ የምናቀው ሲሆን በሌሎች መፅሐፍቶቹም ተወዳጅነትን አትርፏል፡፡ በመሆኑም ዶ/ር ኤሊያስ ገብሩ የወጣትነት ስኬት፣ ጥንካሬዎቹንና ምስክርነቱን ለእናንተ ለአንባቢዎቻችን ሊያደርስ ከቅንድል መፅሄት ጋር በአውደ - ብሩኃን ገፆች ቆይታ አድርጓል፡፡ በአዘጋጅ ነጻነት ጌታቸው እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

ሰናይ ንባብ !

**ቅንድል**፡- ዶ/ር ኤልያስ በመጀመሪያ የቅንድል ዲጂታል መጽሔት የአውደ ብሩሀን ገጽ እንግዳችን ለመሆን ፍቃደኝነትህን ስላሳየህን በአንባቢያን እና በመጽሔታችን ስም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

**ዶ/ር ኤልያስ**፡-እኔም አክብራችሁ ለቅንድል መጽሔት እንግዳነት ስለመረጣችሁኝ የዝግጅት ክፍሉ አባላትን በሙሉ ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

**ቅንድል**፡- ዶ/ር እንግዳችን በመሆን ስለተገኘህ በድጋሚ እንኳን ደህና መጣህ፤ እንግዲህ ወጣት እንደመሆንህ አንተ እያልኩ ነው ምጠይቀው፡፡

**ዶ/ር ኤልያስ**፡-ኧረ ደስ እንዳለሽ አንቺም ማለት ትችያለሽ ወዳጄ (ትንሽ ሳቅ)

ቅንድል፡- እስቲ እኛ ዶ/ር ኤልያስ ማነው? የሚለውን ከምንገልጽ እንዲሁ በአጭሩ ዶ/ር ኤልያስ ገብሩ ማን ነው የሚለውን ለአንባቢያን አስተዋውቅልን

**ዶ/ር ኤልያስ**፡-ኤልያስ እንግዲህ የዚህ ትውልድ አንዱ ሰበዝ ነው፡፡ ባይገርምሽ- በአብዛኛው ሀኪምና ደራሲነቴ ላይ ስለሚያተኩር ሰውኛ እኔነቴን የሚጠይቀኝ የለም፡፡ ያው እንዳልኩሽ እንደዚህ ትውልድ አንድ አባልነቴ ከብዙዎቻችሁ ጋር የምጋራው የኑሮ ድር አለ፡፡ በግሌ ፍቅር፣ ጥበብና ሰላማዊነት ይማርከኛል፡፡ እምም... ኤልያስ .. በተለይ ይህ ትውልድ አቅጣጫ ጠቋሚ ካገኘ ችግሮቻችንን የመፍታት አቅም እንዳለው የሚያምን ሰው ነው፡፡ በእውቀትና እምነት ላይ የተወቀረ ስብእና የትኛውንም የፈተና ተራራ መሻገር ብቻ ሳይሆን ተራራውን መናድም እንደሚችል ያውቃልና ነው እንዲህ ማሰቡ፡፡ የቻለውን ያህል አስተዋጽኦ አበርክቶ ማለፍ ነው እቅዱ፤ ለህዝቡም፣ ለአገሩም ... ለዓለምም... ባጭሩ ይሄ ነው ኤልያስ፡፡

**ቅንድል**፦እሺ እንግዲህ.... ያው አንተም እንደገለጽከው ዶ/ር ኤልያስ ዘርፈ ብዙ ሰው ነው። በሙያው ሀኪም ፣ በስጦታ የብዕር ጥበበኛ ፣ በተግባሩ ለወጣቶች ምሳሌ ነው። ዶ/ር የዚህ ሁሉ መሰረት ምንድነው?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦በግሌ የሁሉም ነገር መሰረት ፈጣሪ እንደሆነ አምናለሁ። ሲፈጥርሽ ገና በዚህ በኩል ነው የምትዘልቂው ካለሽ መንገዱን ራሱ ይጠርግልሻል። ግን ያው ከኛ የሚጠበቅ ነገርም አለ። መንገዱ ቢጠረግም ካልተጓዝሽበት ዋጋ የለውምና። ለመጓዝ ደግሞ መዳረሻን ማወቅ ያስፈልጋል። ማነኝ? ምንድነኝ? ምን አለኝ? መክሊቴ ምንድነው? ድክመቴ ምንድነው? ጥንካሬዬስ? ከየት ነው መነሻዬ? መዳረሻዬስ? እንዴትና በየት ብሄድ ነው ግቤ ጋር የምደርሰው? . . . የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ተቀዳሚው ጉዳይ ይመስለኛል። ከዚያ በኋላ ያለው እቅድ አውጥቶ ጽናትና ትዕግስትን ወደ ሚጠብቅ ትግበራ መግባት ነው። ከምንም በላይ ደግሞ ድካም ሲሰማ ላይ ወዳለው አምላክ ቀና ብሎ ብርታትን መጠየቅ ያስፈልጋል።

**ቅንድል**፦የድርሰት ስራን ስትጀምር ተሰጦኦ ነበረህ ወይንስ በማንበብ ካካበትከውና ከህይወት ትዝብትህ የተረፈ ነው?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ትዝ ይለኛል፤ የሚኒስትሪ ፈተናችንን አልፈን 9ኛ ክፍል የተቀላቀልን ሰሞን አዲሱ የአማርኛ አስተማሪያችን አጭር ልብ-ወለድ ጽፈን እንድንመጣ የቤት ሥራ ሰጠን። እኔ የዚያን ጊዜ መጽሐፍ ማንበብ ብወድም መጻፉ ላይ ግን እንብዛም ነበርኩኝ። ሁላችንም ታዲያ የጻፍነውን አጭር ልብ-ወለድ ለመምህራችን አስገባን። ባይገርምሽ ስለ ተማሪዎች ፎንቃ ምናምን ነበር የጻፍኩት (ፈገግታ) ። እንግዲህ ይታይሽ ክፍሉ ውስጥ ከ50 በላይ ተማሪዎች ነበርን። ከሣምንት በኋላ እኚሁ መምህራችን ወደ ክፍላችን እንደገቡ “ኤልያስ ገብሩ ማነው?” ሲሉ ነበር የጠየቁት። እኔ እንደሆንኩኝ ለማሳየት እጄን ሳወጣ ልብ-ወለድ የጻፍኩበትን ወረቀት አሳዩኝና ለተማሪዎቹ እንዳነብላቸው ነገሩኝ። አጭሩ ጽሑፌን አንብቤ ስጨርስ ግርምት ፊታቸው ላይ እየተነበበ... “ይሄ ለአጭር ልብ-ወለድ ጥሩ ማሳያ ነው። ...አጨብጭቡለት” አሉ። ያኔ ነበር የመጻፍ ተሰጥኦ ይኖረኝ ይሆን? ስል ለመጀመሪያ ጊዜ ራሴን የጠየኩት።

## "...የጋራ ታሪክ የሌለው ህዝብ አንድ አገር ተጋርቶ መኖር ያዳግተዋል።..."

ባይገርምሽ የመጀመሪያውን የስነ-ጽሑፍ ሽልማት የተቀበልኩት የብዙ ምስኪን ኢትዮጵያዊ ህጻናት እናት ከሆኑት ወ/ሮ አበበች ጎበና እጅ ነበር። ገና የስድስተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ነበር በፕላን የልጆች የስነ-ጽሑፍ ውድድር ተሳትፌ ሽልማቱን ለማግኘት የበቃሁት - ሽልማቱን ከሰጡኝ በኋላ አቅፈው ስመው እንዲህ አሉኝ “በርታ ልጄ፤ ፈጣሪ የሰጠህን ችሎታ እንዳታባክነው።” . . . እውነት ለመናገር ግን እኚያ አማርኛ መምህራችን እስኪያስጨበጭቡልኝ ድረስ ደራሲ የመሆን ጠንካራ ህልም አልነበረኝም። ወደ ጥያቄው ስመለስልሽ አንድ ጥሩ ደራሲ የተፈጥሮ ተሰጥኦ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ብዙ የማንበብ ባህልና የኑረቱን ዙሪያ ገባ መታዘብ የሚችልበት ልዩ መነጽርም ያሻዋል። አንዱ ብቻውን በቂ አይደለም። ስለዚህ እኔም የሁሉም ድምር ውጤት ይመስለኛል ወደ ድርሰቱ ያመጣኝ።

**ቅንድል**፦ከድርሰቶችህ በጣም ሰፋ ያለውና ሀገራዊ እይታን፣ ባህልን፣ እምነትንና ሌሎችም ሀገርኛ ጉዳዮችን የዳሰስክበት መጽሐፍ ዋነኛው ኢቶዮጵ ነው። እስቲ የዚህ መጽሐፍ ሀሳብ ጅማሮ እንዴት መጣ?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ ሀገርን የሚያንጻትም የሚያፈርሳትም ዋናው ኃይል ታሪክ ነው። የጋራ ታሪክ የሌለው ህዝብ አንድ አገር ተጋርቶ መኖር ያዳግተዋል። ተቃራኒ የታሪክ አመለካከት ካለው ደግሞ አገር ፈተና ውስጥ ትወድቃለች። በኛም አገር እያየን እንዳለነው ማለት ነው። እናም ኤቶዮጵ መጽሐፍ ስትጸነስ አባቷ የአንድነት ጥማትና እናቷ ደግሞ የትውልድ አብርሆትን መሻት ነበር። እርግጥ ውጥኗ የኔ ብቻም አልነበረም። መንፈሳዊም ዓለማዊም የአዎንታ ኃይሎች ጥንስሱን አብስለውታል።

ቅድስት ምድራችን ኢትዮጵያን መታደግ የሌላ የማንም ሳይሆን የኛ የልጆቿ ኃላፊነት ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ መጀመሪያ ሁላችንንም የምታስማማዋን ኢትዮጵያ ምስል ማርቀቅ ይገባናል። ኢትዮጵያ የ150 ዓመት ሳይሆን ከ5000 ዓመታት በላይ ታሪክ ያላት ሚስጥራዊ ሀገር ናትና ብዙ ማጥናትና ማስተንተን ነበረብኝ።ዋናው ችግር ግን ይህ ትውልድ በሚገባው ቋንቋ ጥበብን ማውረስ ነበርና ዝግጅቱ ፈትኖኛል።

**ቅንድል**፦ ዶ/ር ከዚሁ ከኢቶዮጵ መጽሐፍ ጋር የተያያዘ ጥያቄ ብዙዎች የሚያነሱት በመጽሐፉ ላይ የተጠቀሱት ሀሳቦች በተለይም የሀገራችን ቋንቋ ለአፍሪካ ሀገሮች ስያሜ እስከመሆን የደረሰ እንደነበር ይገለጣል እና ያ ልቦለዳዊ እይታ ወይስ እውነታ የሚሉ አሉ እሱን እንዴት ትገልጸዋለህ?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦አብዛኛዎቹ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ እውነታዎች ናቸው። ወዳጄ ይህ ያለንበት አህጉር አፍሪካ የተባለውኮ ከጥቂት ክፍለ ዘመናት በፊት ነው። ከዚያ በፊት ያሉ የግሪክና የፖርቱጋል ካርታዎች ሙሉ አህጉሪቷን ኢትዮጵያ ብለው ነበር የሰየሙት፤ ኤቶዮጵ ላይ እንዳስቀመጥኩት አፍሪካ የሚለው አዲስ ስያሜ ራሱ የወጣው ከመርከበኛ የአፋር ወንድሞቻችን በመነሳት ነው። ብዙ ብንናገር ሚያምነን እናጣለን እንጂ የኢትዮጵያስ ነገር ሚስጥሩ ብዙ ነው።

**ቅንድል**፦ ዶ/ር ኤልያስ ገብሩን በኢቶዮጵ መጽሐፍ ውስጥ አይተነዋል ይላሉ ሰዎች (ፈገግታ) እውነት ነው አንተን የወከለ ገጸ ባህሪ አለ?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦አብዛኛው ወጣት ኤቶዮጵን ሲያነብ ራሱን የሆነ ገጸ ባህሪ ውስጥ እንደሚያገኘው አምናለሁ። ደራሲዎች ሲጽፉ ደግሞ የግል ህይወታቸው ነጸብራቅ በብዙ መልኩ ይገለጣልና የእኔን የሆኑ ሽርፍራፊዎችን ቢያገኙ የሚጠበቅ ነው። ከሞላ ጎደል ብዙ ጫማዎችን እያጠለቅኩኝ ገጸ ባህሪዎቹ ባህር ውስጥ መዋኘት ነበረብኝ። ሙሉ ለሙሉ እኔን የወከለ ማንነት ግን የለም።

**ቅንድል**፦ የዶ/ር ኤልያስ ገብሩ የህይወት ፍልስፍና ምንድነው?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦የተለመደ ነገር ቢሆንም የህይወት ፍልስፍና የሚለው ጥያቄ ድፍን ያለ ነገር ነው፤ ህይወት ትፈሳለች እንጂ አትገደብም። በየቀኑ የተለያዩ አይነት የህይወት አመለካከቶችን እናካብታለን። ፍልስፍናችን በኑሮ ልምምድና የእውቀት አድማሳችን ልክ እያደገና እየዳበረ የሚመጣ ነገር እንጂ ይሄ ነው ብለን የምንዘጋው ሕገ ደንብ አይደለም። ከምናውቀው የማናውቀው እጅግ ይገዝፋልና። እናም ሁሌም አዲስ እውነትን፣ አዲስ ርዕዮትና ፍልስፍናን ለመመርመር ዝግጁ የሆነ ማንነት ሊኖረን የሚገባ ይመስለኛል።

**ቅንድል**፦ ወጣትነት ምንድነው ላንተ?

ዶ/ር ኤልያስ፦ ማብሰልም፣ ማንደድም የሚችል ፍም እሳትነት ነው። ጥንቃቄና እውቀትን የሚሻ የብርታት ዘመን።

ቅንድል፦፡ ስኬታማ ነኝ ብለህ ታስባለሁ ? ስኬትስ በአንተ እይታ እንዴት ይገለጻል?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ የስኬታማነት መለኪያ የሀብት፣ የማዕረግና የዝና መጠን ሳይሆን ውስጣዊ ሠላምና ደስተኝነት ይመስለኛል። በግሌ ውስጤ በአዎንታዊ እስትንፋሶች የተሞላ ነው። ፍቅር፣ አንድነትና ሰላምን እንግቤ ስለምጓዝ ገና ከጅምሩም ስኬታማ ነኝ ማለት እችላለሁ።

**ቅንድል**፦ እሺ ዶ/ር ቢያ ቶ ኮ / አንድ ሀገር/ የሚል ድርሰት አለህ እናም ባብዛኛው ስራዎችህ ሀገራዊ ይዘት ላይ ያተኩራሉ ይህ ከአንተ ሀገራዊ ስሜት ጋር ይያያዛል?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ ሀገር ከሌለ ምንም የለም። ያፈራከው ሀብት፣ ያገባሃት ሚስት፣ የተማርከው ትምህርት … ሁሉ ዋጋ ያጣል። ምስኪን ሶሪያውያን ከሞቀ ቤታቸው ወጥተው በኛ ጎዳናዎች ሲዳክሩ የምታያቸው ሀገራቸውን እንደ እንቁላል መንከባከብ ስላልቻሉ ነው።



ሀገር ግን እንደ ፈጣሪ ፍጹምና ልዕለ ኃያል ነች ማለትም አይደለም። ለዚያም የህዝቦቿን ሀገራዊ ስሜትና አርበኝነት ትሻለች። አርበኝነቱ አንድነቷን በማስጠበቅ፣ ከጠላት በመከላከል፣ ችግሮቿን በመቅረፍ አልያም በሌላ መልኩ ሊገለጽ ይችላል። እኔም አንድ ኢትዮጵያን እንደሚወድ የዘመኑ ሰው ከምንም በላይ በህዝቦቿ መካከል ያለው መቃቃርና ክፍፍል እንቅልፍ ይነሳኛል። ይህንን እውነታ አንድ ሀገር/ ቢያ ቶኮ የተሰኘው መጽሐፌ ላይ ያሉ ወጎችና ግጥሞችን ያነበበ ሁሉ የሚረዳ ይመስለኛል።
ሀገሬን እወዳለሁ። ሌሎች የሌላቸው ብዙ ጸጋዎች እናት ኢትዮጵያ አሏት። ህዝቦቿ ግን ንቃተ ህሊናችን ብዙ ይቀረዋል፤ ብዙ ሥራ ይጠበቅብናል።

**ቅንድል**፦ ኢትዮጲያ ባንተ እሳቤና አንደበት እንዴት ትገለጻለች ? ኢትዮጲያዊነትስ ምን መሆን ነው ?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ ኢትዮጵያያ ለሚያውቋት ብቻ የምታረብብ መንፈስ ነች። ኢትዮጵያዊነት ደግሞ በመወለድና እዚህ በመገኘት የሚሰጥ ዜግነት ሳይሆን ልብ ላይ የሚታነጽ ማንነት ነው። የገባው ሰው የትም ቦታ ቢሆን፣ የምንም ሀገር ዜግነት ቢኖረው ኢትዮጵያዊነትን ሊታደል ይችላል። ለዚህ ደግሞ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት ራስ-ተፈሪያኖች ናቸው።

**ቅንድል**፦ በአንድ ኢንተርቪው ላይ ሰይፉ ላይ ይመስለኛል ባልሳሳት ስለ ትውልድህ ማለትም በዚህ ዘመን ባሉ ወጣቶች እምነት አለኝ ብለሃል፤ ይህንን ነገር ከወጣቶች ምክንያታዊነት፣ ሀገር ፍቅርና ቅንነት አንጻር እንዴት ትቃኘዋለህ?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ ብዙ ጊዜ የኔ ትውልድ ስል ሌላው የሚረዳው በኔ እድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን ለማለት ይመስለዋል። ባጭሩ ለመግለጽ የኔ ትውልድ የምለው በፍቅር የሚያምን፤ በእውቀትና ክህሎት ራሱን የሚያበለጽግ፤ ከሰፈር ሀሳብ በላይ ዓለም አቀፋዊ ምልከታን የታደለ፤ በሀሳብና በችሎታ እንጂ በዘርና በሃይማኖቱ ማንንም የማይፈርጅ፤ በየዘርፉ በሚያሳየው የሥራ እመርታ አገሩን ማስጠራት የሚችል፤ ጥንታዊነቱን ሳይጥል ዘመናዊው ዓለም ላይ ማንጸባረቅ የሚችለውን ወጣት ነው። ብዙ አስገራሚ ልጆች ያቀፈ ትውልድ ነው ያለን። ወደፊት ትልቅ ኔትወርክ የመፍጠር እቅድም አለኝ። ፈጣሪ ይጨመርበት።

## "...ኢትዮጵያዊነት ደግሞ በመወለድና እዚህ በመገኘት የሚሰጥ ዜግነት ሳይሆን ልብ ላይ የሚታነጽ ማንነት ነው።..."

**ቅንድል**፦ወቅታዊውን የሀገራችንን ሁኔታ እንዴት ትገልጽዋለህ? ከቅርብ ግዜ ወዲህ እኛነት እየጠፋ እኔነት ብቻ እየነገሰ ነው ይህ ቢያ ቶኮ ያልካትን ሀገር አይጎዳትም?

**ዶ/ር ኤልያስ**፦አሁን እየተፈጸመ ያለው ነገር እንደሚከሰት እጠብቅ ነበር። ምክንያቱም የጠላትነት ተረክና ጥላቻን ብቻ እየተማረ ያደገ ትውልድ ለበቀል ሊነሳ እንደሚችል መገመት አያዳግትምና ነው። እርግጥ ነው ሀገራችን ላይ ብዙ ጥፋቶች ተፈጽመዋል። ከኛ ወግና ባህል የወጣ ጭካኔን በዓይናችን አይተናል። ተስፋ መቁረጥ ግን አያስፈልግም። ሠላም፣ ፍቅርና አንድነት ፈላጊ የሆኑ እልፎች አሉ። ዋናው ነገር አንድነትና ፍቅርን የምንሻ ብዙሃን ያገራችንን አብሮነት ማጠናከሩ ላይ መስራት ነው። በተለይ የታዳጊ ትውልድ ሥነ-ምግባር ቀረጻ ላይ ያተኮረ የትምህርት ስርዓትም ያስፈልገናል።

**ቅንድል**፦ በቅርቡ አዲስ ስራ ይዘህ ልትመጣ እየተዘጋጀህ እንደሆነ ሰምተናል። እስኪ ስለሱ አጫውተን።

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ አዎ፤ 25 ግጥሞቼን በሙዚቃና ድምጽ አጅቤ ለአድማጮች አደርሳለሁ። አልበሙን አንድ ፍቅር ነው ያልኩት፤ ቅንብሩን ናትናኤል ሰይፉ ሰርቶታል። በቅርቡ በውጪም፣ ባገር ውስጥም ለገበያ ይቀርባል። እንግዲህ ግጥም በመጽሐፍ መልክ ከሚቀርብ ይልቅ በራሱ በገጣሚው ልሳን ሲነበብ ይመረጣልና ነው ይህን ማድረጌ...

**ቅንድል**፦ በመጨረሻም ለወጣቶች ማስተላለፍ የምትፈልገው መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥህ።

**ዶ/ር ኤልያስ**፦ ወጣቶች ሁልጊዜ አዕምሯችሁ ላይ እንድታተኩሩ እፈልጋለሁ። ለህይወታችሁ ስኬት አንዳች ረብ የማይጨምር ነገር ላይ ጊዜያችሁን አታቃጥሉ። የህይወት ግባችሁን አስምሩ። በምታዩት ነገር ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ ምታዪትን ውጥንቅጥ ወደ መልካሙ መንገድ ለማምጣት ታጥቃችሁ ተነሱ። ከምንም በፊት ግን ራሳችሁ ሰፊ የእይታ አድማስ እንዲኖራችሁ ያሻል። ራሳችሁን መርምሩ፤ ብዙ አንብቡ፣ ተለወጡ።
ይህንን ካረጋችሁ ለሁላችንም ውድ የሆነች፤ በነጻነትና በፍቅር የምኖንርባት፤ በሁሉም ረገድ ሀብታም የሆነች ሀገርን በህይወት እያለን እንደምናይ አምናለሁ።

**ቅንድል**፦ ዶ/ር ኤልያስ እጅግ ድንቅ፣ አስተማሪ ግዜ ነው ያሳለፍነው። ስለነበረን ቆይታ በቅንድል ዲጂታል መፅሔት አንባቢያን ስም አመሰግናለሁ።
ዶ/ር ኤልያስ፦እኔም ከልብ አመሰግናለሁ




# የቅኖች ገፅ



## የሀገር ፍቅርን በተግባር የኖረ ኢትዮጲያዊ

ችግር አለ ከተባለ በችግሩ ቦታ ከሚገኙ ጥቂት የመፍትሄ ሀሳብ ባለቤቶች ውስጥ አንዱ ብቻ ሳይሆን መፍትሄን በተግባር የሚያሳይ የተግባር ምሳሌ ነው። የሀገሩን ፍቅር የሚገልጸው በተዋቡ የቴሌቪዥን አስቱዲዮዎች በመገኘት ለጆሮ የሚስማሙ ቃላት እየመረጠ በማውራት ሳይሆን ከ1000 ኪ.ሜ በላይ እርቀት በመጓዝ ታሪክ የሰሩ ጀግኖችን በማክበር፤ የወገን የሰቆቃ ድምጾችን ሰምቶ ድጋፍ በማሰባሰብ ፈጥኖ በመድረስ ፍቅሩን ኖሮ የሚሳይ ብርቅዬ ኢትጲያዊ ነው ብንል ማጋነን አይደለም። ቅንነት የህይወት መስመሩ ነው፤ ምክንያታዊ ሀሳቦቹ የጥበብ ስራዎቹ መገለጫ ናቸው። የሀገር ፍቅሩ በታሪክ አስተዋሽነቱና ለሁሉም የሀገሩ ህዝቦች ባለው አክብሮትና ፍቅር በተደጋጋሚ ገልጾታል። ማነው ካላችሁኝ ያሬድ ሹመቴ ስል በቅንነት ተምሳሌት አምዳችን ሾመን ልናከብር የወደድነውን ሁለገብ የኪነ-ጥበብና የታሪክ አስታዋሽ እናስተዋውቃችሁ። ያሬድ ሹመቴን የዛሬው የቅንድል መጽሔት ይቅኖች ምሳሉ ለማድረግ የወደድነው ብዙዎቻችን እንደምናውቀው ጉዞ አድዋን በማዘጋጀት ታሪክን ለትውልድ ለማስተማር በተለያየ ግዜ ለሚያከናውናቸው የታሪክ መውድስ ሀገር ፍቅሩን መዝነን በሀገራችን በተለያዩ ግዜያት በሰው ሰራሽ ግጭቶችና የተፈጥሮ አደጋዎች ወገኖቻችን ሲፈናቀሉና ሲቸገሩ ከሌሎች ቅን አሳቢ ኢትዮጲያውያን ጋር በመሆን የምግብ፣ የቁሳቁስ፣ አልባሳትና ሌሎች ሰብዓዊ ድጋችን በማስተባበር ታላቅ ቅንነቱን ለወገኑ ያሳየ የቅን ምሳሌ ስትል ቅንድል ዲጂታል መጽሔት ምስጋናዋን ታደርሳለች።እነዚህን በተቋም ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራትን እንደግለሰብ እያከናወነ ለሀገሩ የሚለፋን ማወደስ ግዴታችን ነውና። እኛም ከጥበብ የተረፈ ስራውን ለሀገሩ ለሰጠው ሀገር ወዳ ኢትዮጲያዊ ክብራችንን እየገለጽን ከዚህ በላይ ለሀገር፣ ለወገን የሚበቃ ትሩፋት የሚያበረክትበትን ዕድሜ እንመኝለታለን።

# የቅኖች ገፅ



## ፈታኙን ተግዳሮት የተጋፈጡት ቅን አሳቢ

ወይዘሮ ዘሚ የኑስ ይባላሉ ተወልደው ያደጉት በመዲናችን አዲስ አበባ ሲሆን ፈታኝ የሚባሉ የህይወትና የዕድገት ግብ ግብ ተጋፍጠዋል። ከአዲስ አበባ እስከ ሮም፤ ከሮም እስከ አሜሪካ ብዙ የህይወት ልምድ ወስደዋል። ታዲያ እኝህን ቅን አሳቢ የዛሬው የቅንድል መጽሔት የቅኖች ገጽ ተመስጋኝ ያረግንበት ዋና ምክንያት ‘‘ ልዩውንና ፈታኙን የኦቲዝም መጋረጃ በመግለጥ ለምን የብርሃን ጮራ እንዲፈነጥቅ አላደርግም?’’  በማለት ወላጆች ለልጆቻቸው ትልቅ ነገር እንደሚመኙላቸው ሁሉ በኦቲዝም ምክንያት ልጅን በእግር ብረት ማሰር ምን ያህል ዘግናኝና ኢ–ሰብአዊ መሆኑን በየአጋጣሚው ማስተማሩን በትጋት ተያይዘው... ጥረታቸው ፍሬ አፍርቶም የሕዝብ ንቅናቄ እንዲፈጠር አድርገዋል። “ጐሽ ለልጇ ስትል ተወጋች” እንዲሉ ሆነና ወይዘሮ ዘሚም ሀገራዊ አጀንዳቸውን ዕውን ለማድረግ ሰለቸኝና ደከመኝ ሳይሉ እልክ አስጨራሽ ውጣ ውረዶችን በማለፍ “ኒያ ፋውንዴሽን” የሚል ተቋም መሰረቱ። በስሩ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በምሥራቅ አፍሪካም የመጀመሪያው የሆነ “ጆይ የኦውቲስቲክ ልጆች ማዕከል” የተባለ ተቋምም አቋቋሙ። የአያሌ ኦውቲስቲክ ልጆችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚለውጥ፤ የእርሳቸው ቢጤ እናቶችን የሕይወት ዘመን ሰቀቀንና ሐዘን የሚቀርፍ ማዕከል በማቋቋም “አበጀሽ” ተባሉ። በዚህ ብቻ ያልተገደቡትና  የምችለውን በጐ ነገር ሁሉ ማድረግ ያስደስተኛል የሚሉት የዘመን ተሻጋሪ ታሪክ ባለቤት የሆኑት ወይዘሮ ዘሚ የኑስ ክቅርብ ግዜ ጀምሮ “ጋዜጠኛ” ሆነው “ያገባኛል” የሚል የሬዲዮ ፕሮግራም በፋና ብሮድካሲንግ ኮርፖሬት ሳምንታዊ የሬዲዮ ፕሮግራም ጀምረዋል። በዚህ ፕሮግራም በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረክ ከፍተው ሰናይ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛሉ። በሌላም በኩል ለኦቲዝም ጉዳይ የተለየ ትኩረት ሰጥተው የመንቀሳቀሳቸውን ያህል ለኦውቲስቲክ ልጆች እናቶችም በአለኝታነት በመቆም በሥራ ፈጣሪነት ቆመዋል። ለዚህም ልጆቻቸው ጆይ የኦውቲስቲክ የልጆች ማዕከል ቢገቡም ባይገቡም በተናጠልም ሆነ በማደራጀት የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችለዋል። ይህ በዚህ እንዳለ መካኒሳ አካባቢ “ስንቅ ቤት” የሚል ፕሮጀክት ነድፈው እውን በማድረግ በተለይ ዕድሜያቸው እስከ ሃያ አራት ዓመት ያሉ ወጣት ሴቶች መጠጊያና የሕይወት ክህሎት ዕውቀት ደሀ ሆነው ወደ ሴተኛ አዳሪነት እንዳይገቡ አርአያነት ያለው ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛሉ። ታዲያ ቅንድል ዲጂታል መጽሔትም እየሰጡት ያለው አገልግሎት ወገን ተኮር በመሆኑ  የቅኖች ምሳሌ በማለት ምስጋናዋን ታቀርባለች።

በርካታ ተቋማት፣ ግለሰቦች የተለያዩ ድጋፎችን እና የቅንንነት ስራን እንደሚሰሩ እሙን ነው እኛም ከበርካቶች መካከል በየግዜው ወደ ቅንነት ተምሳሌት ማጀት እያመጣን ስለምሳሌነታቸው የምናመሰግን ይሆናል እስከዛው ቅኖችን ያብዛልን እንላለን።




**ነዋል አቡበከር**
በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የጋዜጠኝነት እና የኮሚኒኬሽን መምህር
newalabubeker13@gmail.com

# አስገራሚ ባህሎች በዓለም













ብዙዎቻችን ተፈጥሮና ሀይማኖትን ከባህል ጋር ስናምታታ ማስተዋል የተለመደ ነው። ለምሳሌ በፆታ የተከፈለው ባህሪያችን ከእኛነታችን ጋር እጅግ ከመጣበቁ የተነሳ አንዱ የኛነታችን አካል አድርገን እንመለከተዋለን። ባህል ለሴት ልጅ አልያም ለወንድ የከፋፈለው ባህሪም ሆነ ድርጊት ቀስ በቀስ ተፈጥሯዊ በሚመስል መልኩ የተዋሃደን ቢመስልም ከባህል ባህል ከቦታ ቦታ የተለያየ እውነት መኖሩን ስናይ "አጃኢብ" ማለታችን የማይቀር ነው።

ለምሳሌ አንድ ባህልን ልጥቀስ። አንዲት አፍሪካዊ ከተማ ናት። ከዚህች ከተማ ታድያ መኳኳል፣መሽቀርቀር፣ ማጌጥና መዋብ ሁሉ የወንዶች ተፈጥሮ ነው። ንጋት ሳይፈነጥቅ ለፊቱ ቅላት፣ ለእጆቹ ዉበት፣ ለአልባሳቱ ማጌጥ የሚጨነቀው ወንድ ነው። ታዲያ ጥርሱ የበረዶ ያህል ካልነፃ፤ ተክለ ሰውነቱ ካላማረና ንግግሩ ካልጣመ ዋጋ የለውም። ሴቶቹ በበኩላቸው እንደነገሩ ለብሰው በተዘጋጀላቸው ወንበር ይቀመጣሉ። ወንዶች እየተመላለሱ በሚመርጧቸው ሴቶች መሃል ውበታቸውን ያሳያሉ። የቁንጅና ውድድር እንበለው ከፈለግን። የከንፈር ቀለም የተቀባና በወጉ የተሽቀረቀረ፤ የፊት ገፁን ያቀላ ወጣት በሚመለከቱት እንስቶች መሃል ያልፋል-- ለትዳር ሊመረጥ። በዚህ መንደር ለውበቷ መጨነቅ፤ ማጌጥና መኳል የሴቷ ድርሻ አይደለም ። የወንድየው እንጂ።

ባህል ምንም እንኳን በግል ማንነታችን ላይ የራሱን ጡብ ቢያስቀምጥም የኛ ፍላጎትና ምኞት፤ የምንኖርበት አካባቢ እና ሁኔታ በባህላችን ማንነት ውስጥ ትልቅ ሚና አላቸው። በተለይም መልካም ፀጋንና ጤንነትን አጥብቀን የመፈለጋችን እውነት የተለያዩ ባህላዊ ድርጊትን እንድንላመድ ያደርገናል። ምንም እንኳ ይህን ፀጋ ፍለጋ የሚደረጉ በርካታ ጤናማ ባህሎች ቢኖሩም አንድ ለየት ያለውን ደግሞ እዚህ ጋር እናንሳ። ህፃናትን በሁለት እጅ መዳፍ መሃል አስገብቶ እየወረወሩ መቅለብ ብዙዎቻችን ህፃናትን የምናጫውትበት መንገድ ነው። ህፃናቱም ይወዱታል። ከወደ ህንድ ስላፑር ያገኘነው መረጃ ግን ነገሩ ከዚህ ይለያል። ህፃን ልጅ ሲወለድ እድሉ እንዲያምር፤ ክፉ እንዳይነካውና ጤነኛ ህይወት እንዲኖረው በሚል 50 ጫማ ርዝመት ካለው ህንፃ ላይ ቁልቁል ይወረውሩታል።ታዲያ ህፃኑ ቁልቁል ከህንፃው ሲምዘገዘግ ከስር ልጁ መሬት እንዳይወድቅ ጨርቅ ይዞ የሚጠበቁ በርካታ ሰዎች ይኖራሉ።(የወላድ አንጀት እንዴት ያስችላት ይሆን??)

የህፃናትን ነገር ካነሳን አይቀር ወደጃማይካ ጎራ እንበል። በጃማይካ፣ በቻይናና በህንድ አንዳንድ አካባቢዎች እናት ልጅ በምትወልድበት ወቅት "የእንግዴ ልጅ " እየተባለ የሚጠራውን ከሆዷ የሚወጣ አካል መመገብ የባህሉ አንድ አካል ነው።።

ኢንዶኔዥያውያን በተለይም ከሰው ሞት ጋር በተያያዘ አስገራሚ ባህሎች አሏቸው። ለምሳሌ አንድ የቤተሰብ አባል ሲሞት፣ የጐሣው አባል የሆነች ሴት ከዓይኖቿ የፈሰሱት እንባዎች፣ የልቧ ማዘንና መረበሽ በቂ አይደለም። የመንፈስ ህመም ብቻም በቂ አይደለም ብለው የሚያምኑት የዳኒ ጎሳ አባላት ሴቶች ጣቶቻቸውን መቁረጥ እንዳለባቸው ያምናሉ። እናም ጣቶቿን ይቆርጣሉ። በዚህም በመናፍስት ምክንያት ከሚመጣው መቅሰፍት እንድናለን ብለው ያምናሉ።

#አጃኢብ

እዚያው ኢንዶኔዥያ እንቆይ። በእኛ ሀገር ባህል አንድ ሰው ሲሞት ደረት ቢደቃ "ዋይ" ቢባልና ቢለቀስም ሟቾችን መቅበር በተቻለ ፍጥነት ሚደረግ ተግባር ነው። በኢንዶኖዢያ የሚኖሩ የቶረጃ ነዋሪዎች ግን የሞተን ሠው እንደመቅበር የሟችን ሬሳ በዉብ እና የተመረጠ ልብስ አስዉበዉ (ልክ ሠርግ ወይም ልዩ ዝግጅት ላይ እንደሚታደም) ሰውነቱ በሚገባ አፅድተው ከቤት ዉስጥ በክብር ያስቀምጡታል። አብረውትም ይኖራሉ። ሙት አካሉ እዚያው በሚቆይበት ወቅትም እንደሚሰማና እንደሚያይ ታስቦ የቤተሰቡ አካል እንደሆነ ይቀጥላል።(ለአንድ ኢትዮጵያዊ ከሙት ጋር ውሎ ማደር ምን አይነት ስሜት ሊፈጥር እንደሚችል ማሰብ ከባድ አይሆንምን?) ግን ባህል ነው!
ማኅበረሰብ በባህሉ ሲገለጥ ብዙ የሚከበር እና በመልካም እሴቶች የሚልቅ ልኬት ይኖረዋል። አንድ ማኅበረሰብ ለራሱና ለሌላው የሚሰጠው ክብር ለእምነቱና፤ ለእውነት በሚሰጠው ቦታ ባህሉን ልንለካው እንችላለን። አንዳንድ ማኅበረሰቦች ባህላቸው የሰውን ልጅ ብቻ ሳይሆን እንስሳንም ጭምር የሚያከብሩበት ስነ ስርዓት ያስተምራቸዋል። በባንኮክ ታይላንድ ይህ ይንፀባረቃል። ድንገት ወደ ታይላንድ ብታመሩና ከ3000 ኪ.ግ በላይ ፍራፍሬና አትክልቶች የሚስተናገዱበት የምግብ ብፌ ፌስቲቫል ብትመለከቱ እንዲች ብላቹ ወደ ቀረበው ምግብ እንዳትጠጉ። ዝግጅቱ በየዓመቱ ህዳር የሚካሄድ የምግብ ድግስ ነው። ምግቡም የሚቀርበው ለጦጣዎች ነው። አዎ ጣፋጭ እና ትኩስ ፍራፍሬዎች በወግ በወጉ ተደርድረዉ የሚጠብቁት ጦጣዎችን ሲሆን በጥቂት ሰዓት ውስጥ ብዙ ቁጥር ያላቸው ጦጣዎች የቀረበላቸውን ምግብ ለመመገብ ወደ ቦታው ይመጣሉ። ምንም እንኳ ገንፎ አገንፍቶ፣ በቂቤ አጥለቅልቆ ጅብን ለሚያበላ ኢትዮጵያዊ ይህ ብዙ ላያስገርም ይችል ይሆናል። ነገር ግን ይህን ጦጣ የመመገብ ዓመታዊ ትርኢት ለመታደም ወደ ከተማይቱ የሚጎርፈው የጐብኚ ብዛት መመልከት የበለጠ ሳያስገርመን የሚቀር አይመስለኝም።
ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ባህል ባስቀመጠው ልኬት ለመሰፋት ብቻ ሲባል የሰውነትና የፍትህ ገመድ የሚበጥሱ ባህሎችም አሉ። ወንድ ልጅ ክብሩን በባህሉና በማኅበረሰቡ ዘንድ ለማስጠበቅ ሲል ነፍስ እስከማጥፋት ሊደርስ ይችላል። ወደ ኢራንና አንዳንድ የቱርክ ቦታዎች ብናቀና ከማኅበረሰቡ ስነ ስርዓት ውጪ የፍቅር ግንኙነት የመሰረተች ወይም ቤተሰቡን የሚያሳፍር ድርጊት ያደረገች ሴት በቅርብ ቤተሰቧ ተወግራ አልያም በሽጉጥ ተመታ ትገደላለች። ይህ ድርጊት እንደወንጀል መቆጠር የጀመረውም በቅርብ ነው ለዚያውም መንግስታቸው ወንጀል ስለመሆኑ ሳይዋጥለት።

ወደ ጀርመን እናቅና። በእርግጥ በየትኛውም ዓለም የጋብቻ እና የዕድሜ ነገር የተያያዘ ነው። ኢትዮጵያዊያን ገና በጨቅላነት እድሜያቸው የሚዳሩ ከመሆኑም በላይ ከሚቀመጥላቸው የዕድሜ ሰንጠረዥ ባያልፉ አጥብቆ ይከጀላል። በጀርመናውያን ዘንድም በ30 ዓመት እድሜው ያላገባ ወንድ የ30 አመት ልደቱን ሲያከብር የከተማ መንገድ ወይም የህንፃ ወለል እንዲያፀዳ ባህሉ ያስገድደዋል። ሴቷ በበኩሏ ወደ ጓደኞቿ በማምራት አስቸጋሪውን የበር እጀታ የማፅዳት ሂደት ያለ ማጠቢያ መሳሪያ እንድትከውን የግድ ይላታል።(ታድያ ይህን ቅጣት ለማስቀረት ሴቷ ወይም ወንዱ በተቃራኒ ፆታ አንድ ግዜ ቢሣሙ በቂ እንደሆነ ይነገራል።)

ሰው ተብለን ስንበቃ፤ ከዘር እና ቀለም ስንለጥቅ እንደ ማኅበረሰብ አንዱን ከሌላው የሚያስተሳስረው ትልቁ ፀጋ ባህል ነው። በእርግጥ እንደ ኢትዮጵያ ካሉና እጅግ ልዩ ልዩ በሆኑ ባህላዊ ክንዋኔዎች የተሞላች ሀገር እየኖሩ ስለ ባህል ምንነት ማስረዳት አስፈላጊነቱ እምብዛም ባይሆንም ነገር ግን ባህላችን የአስተሳሰባችን አባት፣ የአኗኗር መንገዳችን ፈጣሪ፣ የማንነታችን ጠፍጣፊና ሠሪ ከመሆኑም በላይ "እኛ" በምንለው ማንነት ውስጥ ትልቅ ሚና የሚይዘው ባህል ነው። ታዲያ ባህላችን እርስ በእርስ አስተሳስሮ የሚያቆየን ትልቅ ማገር ቢሆንም የምንኮራባቸው ሊቀጥሉና ትሩፋት ሊሆኑ የሚገባቸውን ጠብቆ ማቆየት፤ የማይጠቅሙ እውነትንም ፍትህንም የሚጫኑትን ደግሞ መተው መልካም ነው ባይ ነኝ። ቸር ሰንብቱ!




የተከበራችሁ እና የተወደዳች  የቅንድል ዲጂታል መፅሄት አንባቢያን እና ቤተሰቦች ሰላም! እንደሚታወቀው ቅንድል መፅሔት በቅጽ -2 በቁጥር 3 ላይ በልዩ አቀራረብ ከተካተቱት ውስጥ አንዱ የጥያቄ እና መልስ ውድድር ነው፡፡ በመሆኑም በቅጽ-2 በቁጥር 3 መፅሄታችን ውስጥ የተጠየቁት ጥያቄዎች ፣ የጥያቄዎቹ መልስና መልሱን በትክክል የመለሱ መላሾች ብሎም ተሳታፊ የነበሩ የቅንድል ቤተሰቦች ከዚህ ከጥሎ ይቀርባሉ፡፡

የቅንድል መፅሔት ቅፅ 2 ቁጥር 3 የልዩ ሽልማት ጥዳቄዎች የነበሩት-

1. በኢትዮጲያ ውስጥ በሚገኙ ገጠራማ አካባቢዎች ከ 30 በላይ ትምህርት ቤቶችን ያስገነባው እውቁ የኪነ-ጥበብ ሰው ማን ይባላል?
2. በኢትዮጲያ የመጀመሪያውን ረጅም ልብ-ወለድ የተጻፈው በማን ነበር? የመጽሐፉስ ዕርስ ምን ይባላል?
3. በኢትዮጲያ እና በጣልያን መካከል በነበረው ጦርነት ወቅት ለጣልያን መረጃ ሰጪ በመምሰል ኢትዮጲያንን ሲያግዝ የነበረው (double agent ) በመባል የሚታወቀው ኢትዮጲያዊ ግለሰብ ማን ይባላል?

የጥያቄዎቹ መልስ

1. በኢትዮጲያ የተለያዩ ገጠራማ ቦታዎች ወንድሙን እና ጓደኞቹን በማስተባበር ትምህርት ቤት ያስገነባው ቅን አሳቢ ግለሰብ ተወዳጁ አርቲስት ዘለቀ ገሰሰ ይባላል፡፡
2. በኢትዮጲያ የመጀመሪያውን ረጅም ልብ ወለድ የጻፉት ግለሰብ ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረየሱስ ሲሆኑ መጽኀፉም ‹ጦቢያ› ይሰኛል፡፡  ነጋድራስ አፈወርቅ ገብረየሱስ ከፀሀፊነት ባለፈም አምባሳደር በመሆን አገልግለዋል፡፡
3. በኢትዮጲያ እና በጣልያን መካከል በነበረው የጦርነት ወቅት ለጣልያን መረጃ ሰጪ በመምሰል ኢትዮጲያን ሲያግዝ የነበረው (double agent ) በመባል የሚታወቀው ኢትዮጲያዊ አርበኛ ባሻየ አዋሎም ሀረጎት ይባላል፡፡

ትክክለኛውን መልስ በቅድሚያ ያገኙ መላሾች ስም እና አድራሻ

1. ሙላለም አበበ.................................ከደብረ ብርሀን
2. የበላይ ንጋቱ .................................ከሀዋሳ
3. የትምጌታ ከንፈ........................ ከአርባ ምንጭ
4. ናርዶሶ በፍቃዱ ........................ ከአዲስ አበባ
5. ሱመያ ያሲን ........................ ከአዲስ አበባ
6.በረከት ማሞ........................ ከላሊበላ
7. ሀና አንጋሳ ............................ ከአዲስአበባ
8. ናትናኤል ሙሉጌታ .................. ከወላይታ ሶዶ
9. ዮርዳኖስ ዘገየ........................ ከወልዲያ
10. ምህረት አብ ግዝሙ................ ከአዲግራት

**ይሳተፉ ይሸለሙ**

ውድ የቅንድል ዲጂታል መፅሔት ቤተሰቦች በሁለት ዘርፎች የበዓል ልዩ  አሸላሚ ውድድሮችን ይዘንላችሁ መጥተናል።

**በስነ-ፅሁፍ ዘርፍ**
ቅንነትን የሚሰብኩ፣ ሀገር ፍቅርን የሚያሰርፁ ፣ ምክንያታዊነትን የሚያስተምሩ ፣ አንድነትን የሚያበረታቱ ግጥሞች ፣ አጫጭር ፅሁፎች(ከ 4000 የሆሄ ብዛት ያልበለጡ) ፤


**በስዕል እና በፎቶግራፍ ዘርፍ**
ኢትዮጲያዊነትን፣አብሮነትን፣ ፍቅርን የሚገልፁ ፤ የሀገራችንን ውብ ባህል  የሚያሳዩ ፤ የምትኖሩበትን አካባቢ ውብ ተፈጥሮ የሚያስተዋውቁ ስዕሎች እና ፎቶዎችን አወዳድረን የአዲስ አመት ሽልማት ለመሸለም ዝግጅታችንን አጠናቀናል።

**የውድድሩ ማብቅያ ቀን**
✔ ውድድሩ ጳጉሜ 5-2012 ያበቃል።

✔️**አሸናፊዎች**
 የዶ/ር ኤሊያስ ገብሩ መፅሐፍ የሆነውን እና የፀሀፊው ፊርማ ያረፈበትን አንድ ሐገር/ቢያ ተኮ የተሰኘ መፅሐፍ ይሸለማሉ።
እንዲሁም መስከረም ላይ በምትወጣው የቅንድል ዲጂታል መፅሔት  ቅፅ-2 ቁጥር-5 ዕትም ላይ አሸናፊዎች እና ስራዎቻቸው ይቀርባሉ።

❗ተወዳዳሪዎች ስራዎቻችሁን ስትልኩ ሙሉ ስም እና አድራሻዎቻችሁን አያይዛችሁ መላክ ይኖርባችኋል።
❗ለ ክልል ተወዳዳሪዎች ሽልማታችሁን ባሉበት ቦታ በፖስታ ቤት የምንልክ ይሆናል።

✔️**ስራዎቻችሁን ከዚህ በታች👇 ባሉት አማራጮች ልትልኩልን ትችላላቹ።**
ቴሌግራም፡-  http://t.me/KendelM
ፌስቡክ፡- http://m.facebook.com/kdigitalmagazine/
ኢሜል-  Kdigitalm agazine@gm ail.com



#ቅምሻ



# የዛሬ 36ኣመት ገደማ

**በ ዶ/ር ቢኒያም ግርማቸው**

ከኮሌጅ ተመርቃ የ 22 ዓመት ልጅ እያለች "WJZ-TV" የሚባል የቴሌቪዥን ጣብያ ውስጥ በዜና አንባቢነት ተቀጥራ ትሰራ ነበር። በወቅቱ በዛ ቴሌቭዥን ጣብያ በእድሜ ትንሿ እና ብቸኛዋ ጥቁር አሜሪካዊ ዜና አንባቢ ነበረች። ነገር ግን "....ለቴሌቪዥን የሚሆን መልክ የለሽም! ብዙም አትመስጪም! ተመልካች ሳቢም አይደለሽም! ፀጉርሽ ሉጫ አይደለም! ብቃትሽም ቢሆን እምብዛም ነው! በተደጋጋሚ ዜና ስታነቢ ቃላቶችን በተሳሳተ መንገድ ስትጠሪ ታዝበናል!...." ብለው የቴሌቪዥን ጣብያው አመራሮች በመጀመርያ ከስራ ዝቅ (Dem ote) እንድትደረግ ያደርጉና ከዛም ከስራ ገበታዋ ያባርሯታል።

Fast forward! (አሁን ላይ!)
በሚገባ ውሃ፣ መብራት እና መፀዳጃ ቤት እንኳን የሌለው ቤት ውስጥ ያደገችው፣ ነጮችን በቤት ሰራተኝነት ከሚያገለግሉት አያቷ ጋር ልጅነቷን ያሳለፈችው፣ እጅግ በጣም ስኬታማ ከሆነች የቤት ሰራተኛ (Maid) ነው የምትሆነው ተብሎ በቤተሰቦቿ የተተነበየላት፣ በገዛ አጎቷ እና በዘመዶቿ ወዳጆች አካላዊ እና ፆታዊ ጥቃቶች የደረሰባት፣ ገና በ 9 ዓመቷ በአሰቃቂ ሁኔታ የተደፈረችው፣ ድጋሚ በ 14 ዓመቷ ተደፍራ፣ አርግዛ ከዛም ልጇ "prem ature" ስለነበረ የሞተባት፣ በግፍ አትችይም ተብላ ከቴሌቪዥን ዜና አንባቢነት የተባረረችው "Oprah Winfrey" ዛሬ ላይ "የቴሌቪዥን ቶክ ሾዋ ንግስት(Queen of television talk shows)" በሚል ቅፅል ስም ነው የምትጠራው አባዬ! የሷን ያህል በቲቪ "Talk show" ዘርፍ ስኬታማ የሆነ ማንም ሰው የለም። ለወደፊትም ይኖራል ማለት ከባድ ነው! ምክንያቱም "ሚልየነር" ሳይሆን "ቢልየነር" ሆናበታለች! ሴትየዋ 2.7 ቢልዮን ዶላር ብቻዋን ታወጣለች! አሜሪካ ብትሄድ ብቸኛዋ ጥቁር ሴት ቢልዮነር እሷ ናት።በ "University of Pennsylvania" "History 298: Oprah Winfrey, the Tycoon" የሚባል ኮርስ እንደሚሰጥ ታውቃለህ አባዬ? ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች "ኦፕራ እንዴት ሃብታም ልትሆን ቻለች?" የሚለውን ይመረምራሉ ስልህ!😀 በነገራችን ላይ በጣም የምትታወቅበት "The Oprah Winfrey Show" ለ 25 ዓመታት ከ "Septem ber 8, 1986" እስከ "May 25, 2011" የተላለፈ ሲሆን በአሜርካ የቴሌቪዥን ታሪክ ትልቅ የተመልካች "rating" ያለው እንደሱ የለም! "Oprah" የመጀመርያዋ የራሷ ሾው አዘጋጅም ፕሮዲውሰርም መሆን የቻለች ተዓምረኛ ሴት ናት። ዛሬ ላይ በተለያዩ የቴሌቪዥን ጣብያዎች ላይ የምታያቸው የ"Talk show"ፕሮግራሞች የተገለበጡት ከሷ እና ከ "David Letterm an" ነው! ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ! ለ 25 ዓመታት የተላለፈው "The Oprah Winfrey Show" "4561" ክፍሎች (Episodes) አሉት! Who does that?😳 እነዚህን ክፍሎች አውርደህ በቀን እንኳን አንድ ክፍል ብታይ በ 12 አመት ነው የምትጨርሰው! አባዬ እንዳትሞክረው!😀። "Oprah Winfrey" ድንቅ፣ ጠንካራ፣ ብርቱ፣ ዐርዓያ፣ ተምሳሌት፣ ጀግና፣ ሃብታም እና ለብዙ ዜጎች ስራ ፈጣሪ በመሆንዋ በ 2013 የሃገሪቷን ከፍተኛ የክብር ሽልማት(Presidential Medal of Freedom ) በወቅቱ የሃገሪቷ ፕሬዝዳንት ከነበሩት "Barack Obam a" የተቀበለች ሴት ናት። በነገራችን ላይ ምን ያህል ተፅህኖ ፈጣሪ እንደሆነች የምታውቀው በ 2008 የአሜሪካ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ 1 ሚልዮን የሚሆኑ መራጮች ድምፃቸውን ለ "Barack Obam a" እንዲሰጡ ያደረገች ሰው መሆንዋን ስታውቅ ነው።

#ቅምሻ

በመጨረሻም አንድ ገጠመኟን ላጋራችሁ እና ልውጣ! "Oprah Winfrey" እጅግ በጣም ሃብታም ከሆነች በኃላ በአንድ አጋጣሚ ወደ "Switzerland" ታቀናና ውድ ውድ የቅንጦት ቦርሳዎች የሚሸጡበት ሱቅ ውስጥ ትገባለች። ከዛም ቦርሳዎቹን ስትመለከት አንድ የተሰቀለ ቦርሳ ቀልቧን ይስበዋል። በወቅቱ ሱቅ ውስጥ ያለችውን ሻጭ "...ያንን ቦርሳ አሳይኝማ!...." ስትል ትጠይቃታለች። ልጅቷም "...አንድ አሮጊት ሴት ሲጀመር ተሳስታ ይሆናል እንጂ እንደዚህ አይነት ሱቅ ውስጥ ልትገባ አትችልም! በዛ ላይ ጥቁር ናት! አሰብኩት እኮ አንዲት ጥቁር ሴት መሰረታዊ ፍላጎቷን አሟልታ የ 38 ሺህ ይሮ ቦርሳ ስትገዛ?!" ትልና "...ይቅርታ እሱ ይወደድብሻል !...ሌላ ርካሽ ቦርሳዎች አዛ ጋር አሉልሽ እነሱን ማየት ትችያለች!..." ትላታለች! አባዬ! አይደለም ቦርሳውን የቦርሳውን አምራች ኩባንያ እንደ ቀልድ መዥለጥ አድርጋ መግዛት የምትችለው "Oprah" ዘረኝነትን ሚልየነር ወይም ቢልየነር ስለሆንክ/ስለሆንሽ የሚጠፋ ነገር ሳይሆን ለረጅም ግዜያት የሰዎች አመለካከት ላይ በመስራትን የሚጠፋ ነው ትላለች!

"....Surround yourself with only people who are going to lift you higher!..."
Oprah Gail Winfrey
ሌሎች መሰል አነቃቂ ፅሁፎችን "ሰው ሁን ከሰውም ሰው ሁን" ( @EthioBini) የቴሌግራም ቻናል ላይ ያገኛሉ።

DIGITAL MAGAZINE

FaceBook Search @KDigitalMagazine

Telegram Search @KendelM

#አዕምሮ ጤና



ፊራኦል መስፍን
በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የአዕምሮ ሀኪም እና መምህር
firaolmesfin8@gmail.com



# ሰዎች ራሳቸውን ለምን ያጠፋሉ?

በዓለማችን ላይ እራሳቸዉን የሚያጠፉ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነዉ። ራሳቸውን ከሚያጠፉ ሰዎች መካከል (ህጻናት እና ወጣቶችን ጨምሮ) 90 ከመቶ የሚሆኑት በአእምሮ ህመም የሚሰቃዩ ሰዎች እንደሆኑ ይታሰባል በተለይም በድባቴ ህመም, በባይ ፖላር ህመም እና በስኪዞፍሬኒያ የተጠቁ ሰዎች እንዲሁም የአልኮል መጠጥ ወይም ሌላ ሱስ ያለባቸው ሰዎች ከሌሎች በበለጠ ራሳቸውን ለማጥፋት የተጋለጡ ናቸው።

የአእምሮ ህመም የሌለባቸው ሰዎች ደግሞ በጊዜያዊ የስሜት ነውጥ ምክንያት ወይም ለረጅም ጊዜ በህመም በሚያሰቃይ አካላዊ ህመም በመማረር እራሳቸውን ለማጥፋት ሊሞክሩ ይችላሉ።

ህጻናት ልጆች ሰው ሞቶ የሚቀር ስለማይመስላቸው በቀላሉ እራሳቸዉን ለመጉዳት ሊገፋፉ ይችላሉ።

ሰዎች ራሳቸውን ለማጥፋት የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ ለምሳሌ በሃገራችን የተለመዱ ራስን የማጥፊያ መንገዶች ራስን መስቀል ፣ መርዝ መጠጣት ፣ ወንዝ ውስጥ መግባት እንደሚሆኑ ይገመታል።

አብዛኛውን ጊዜ ራሳቸውን ለማጥፋት ሃሳብ/ዕቅድ ያላቸው ሰዎች ይህን ሃሳባቸውን የሚጠቁም ፍንጭ ለቤተሰብ አባላት ፣ ለጓደኛ ፣ ለመምህር ወይም ለሃኪም ይሰጣሉ።

እነዚህም የማስጠንቀቂያ ምልክቶች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፦

1.የትምህርት አፈጻጸም በድንገት ማሽቆልቆል - ከዚህ በፊት በትምህርታቸው ታታሪ የነበሩ ተማሪዎች የትምህርት እንቅስቃሴያቸው ሲዳከም ፣ ከክፍል መቅረት ሲያበዙ

2.ስለሞት ወይም ራስን ስለማጥፋት ደጋግሞ ማንሳት - በንግግር ፣ በጽሁፍ ወይም በስዕል ይህንን ስሜት ደጋግመው ሲያንጸባርቁ

3.ድንገተኛ የባህሪ መለዋወጥ - ገለልተኛ ፣ ብቸኛ ወይም ብስጩ መሆን ፣ ወይም ሌሎች አስቸጋሪ ባህሪያትን ማሳየት መጀመር

4.ጥሩ ያልሆኑ ጓደኞች መያዝ - ከዚህ በፊት ከማይቀራረቧቸውና ዕጽ እንዲሁም አልኮል ከሚጠቀሙ ልጆች ጋር አዲስግንኙነት ሲመሰርቱ

5.ጤናማ ያልሆነ የቤተሰብ ግንኙነት - የአካላዊ ጥቃት ምልክቶች - ተማሪው/ግለሰቡ ላይ ተደጋጋሚ የሆኑ የአካላዊ ጥቃት ምልክቶች ሲታዩ ፣ ለምሳሌ ያበጠ ወይም የበለዘ ፊት

6.ለአደጋ የሚያጋልጡ ባህሪያት ማሳየት - ከተለያዩ ሰዎች ጋር የጾታ ግንኙነት ማድረግ ፣ አልኮል እና እጾችን መጠቀም ፣ እንደቅሚያ ያሉ አስተኛ ወንጀሎች ላይ መሳተፍ

7.በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደርስ ጥቃት ሰለባ መሆን - ትምህርት ቤት ውስጥ የሚፈጸሙ አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጥቃቶች ሰለባ መሆን

8.የድብርት ህመም ምልክቶችን ማሳየት

አስቸኳይ እርምጃ የሚፈልጉ ምልክቶች:

ራስን ስለ ማጥፋት በግልጽ መናገር ወይም መጻፍ

ቃል በቃል “ብሞት ይሻለኛ ነበር”፣ “በህይወት መኖር ምን ዋጋ አለው?!” የመሳሰሉ አባባሎችን መጠቀም

ራስን ማግለል- ከቤተሰብ ፣ ከጓደኛ ፣ከማህበራዊ ተሳትፎ :


ራስን የማጥፊያ መንገድ ማዘጋጀት

ራስን የማጥፋት ሃሳብ ፣ ዕቅድ እና ሙከራ እንዴት መከላከል ይቻላል?

መምህራን ምን ማድረግ ይችላሉ?

ራስን ስለማጥፋት መጠየቅ
እራስን ስለማጥፋት ግለሰቡን መጠየቅ ግለሰቡ እራሱን የማጥፋት ሃሳብ እንዲኖረው አያደርግም። ይልቁንም ግለሰቡን እራስን ስለማጥፋት መጠየቅ እንዲህ ያለሀሳብ ይኑረው አይኑረው አውቆ የመከላከል እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ብቸኛ መንገድ ነው። ጥያቄውን በተለያዩ መንገዶች ማቅረብ ይቻላል ፤ ለምሳሌ ያህል፤
በተኛሁበት በቀረሁ የሚል ስሜት ተሰምቶሽ ያውቃል?
መኖር ዋጋ የለውም የሚል ስሜት ተሰምቶሽ ያውቃል?
በኑሮዬ የሚያገጥሙኝ ችግሮች አስቸጋሪና መፍትሄ የሌላቸው ስለሆኑ ሞቼ ብገላገል ይሻለኛል የሚል ስሜት ተሰምቶሽ ያውቃል?
ግለሰቧ ከእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ለማንኛቸውም አዎን የሚል ምላሽ ከሰጠች "እራስሽን ለመጉዳት ዕቅድ አውጥተሻል?" ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል ፤ይህም የአደጋውን ክብደት ለማወቅ ይረዳል።
አስፈላጊውን እርማጃ ለመውሰድ ዝግጁ መሆን
ራሱን ለማጥፋት ከፍተኛ ዕድል ያለውን ሰው ብቻውን አለመተው ፣ እርዳታ እስኪያገኝ ድረስ አብሮ መሆን
ከሌሎች መምህራን ፣ ከቤተሰብ እና የህክምና ባለሙያዎች ዕርዳታ መጠየቅ ባስቸኳይ ወደ ህክምና ተቋም መውሰድ
ቤተሰብ ምን ማድረግ ይችላል?
ግለሰቡ አደጋ ላይ እንደሆነ መረዳት
ራሱን ለማጥፋት ከፍተኛ ዕድል ያለውን ሰው ብቻውን አለመተው ፣ እርዳታ እስኪያገኝ ድረስ አብሮ መሆን
አስፈላጊውን እንክብካቤ መስጠት
ራስን ለማጥፋት የሚሆኑ ነገሮችን ካካባቢው ማራቅ
ባስቸኳይ ወደህክምና ተቋም መውሰድ
ዉድ አንባቢያን ለዛሬ እዚህ ላይ አበቃሁ ! ቸር እንሰንብት

ቅንድል DIGITAL MAGAZINE
**ቅንድል መፅሔት በፌስቡክ :- @KDigitalMagazine**
**ቅንድል መፅሔት በቴሌግራም :- @KendelM**
**አሁኑኑ የቤተሰባችን አባል ይሁኑ!**



# እራስዎን እና ቤተሰብዎን ከኮሮና ቫይረስ ይጠብቁ !

## ባለመዘናጋትዎ ህይወት ይታደጋሉ !

- ኮሮና መድሀኒትም ሆነ ክትባት ያልተገኘለት ገዳይ ቫይረስ ነው
- ፊትዎን ባልታጠበ እጅ ባለመንካት ፣ ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ባለመገኘት ፣ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ በአግባቡ በማድረግ ከቻሉም ከቤት ባለመውጣት ራስዎን ይጠብቁ!



አናናስ ግርማይ
የሥነ-ማህበረሰብ ባለሙያ
britanitam@gmail.com

# ማን ነው አትችይም ያለሽ?

የፆታ እኩልነት ሰብአዊ መብት ቢሆንም በአለም ያሉ ሴቶች በኢኮኖሚ ተሳትፎ፤ መሰረታዊና ከፍተኛ የትምህርት እድል፤ የፖለቲካ ውክልና፤ ጥሩ የጤና አገልግሎት እና ከአደጋ ጥበቃ በማግኘት በኩል ከወንዶች እጅግ ያነሰ እንደሆነ ብዙ ጥናቶች የሳያሉ። የሴቶች መብትን ማክበርና በውስጣቸው ያለውን አቅም ማውጣት እንዲችሉ እኩል እድል ማግኘት የሚስፈልጋቸው የፆታ እኩልነት ለማምጣት ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ የልማት ግብን ለመምታት ይጠቅማል።
በኢትዮጵያ ከጠቅላላ ህዝብ 80% በገጠሩ ክፍል የሚኖረው ሲሆን አብላጫውን የግብርና ጉልበት የሴቶች ቢሆንም ምንም አይነት እውቅና ስለማይሰጠው ግብአቶቹ እና የህብረተሰብ ተሳትፎ ሁሉ በአባት ወይም በባል ቁጥጥር ስር ይውላል። ከሦስት ሴቶች አንድዋ አካላዊ፤ስነልቦናዊና የወሲብ ጥቃት ይደርስባታል፤ 65% ሴቶች ግርዛት ያስተናግዳሉ፤ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ከገቡ ሴት ህፃናት ውስጥ ግማሹ ብቻ 5ኛ ክፍል መድረስ ይችላሉ። (Gender Equality and Women Empowerment /Ethiopia/USAID-2020).
ወደ ርዕሴ ስመጣ ከላይ ያሰቀመጥኩት እውነታ በሴቶች እለት ተእለት እንቅስቃሴ ላይ ትልቅ ተግዳሮት እንደሆነ ግልፅ ነው። ሆኖም ግን ይህን ከባድ ጫና ተቋቁመው እና እኩል እድል መጠቀም እንዲችሉና ወደ (Equty) እንዲመጡ ቢደረግ ከውንድም በላይ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ያሳዩ በርካታ ሴቶች አሉ፤ ይህም የይቻላል ስሜትን ይፈጥራል። በአሁኑ ሰዓት የፆታ እኩልነት እንዲመጣ በሰፊው እንቅስቃሴ እየተደረገ ቢሆንም ሴቶች ተወዳዳሪ ሆነው በከፍተኛ ባለሞያነት ፤በኢኮኖሚውና እና በፖሊቲካው ያላቸው ተሳትፎ ካላቸው ቁጥር ጋር ሲወዳደር እዚህ ግባ የሚባል አደለም። እዚህ ላይ ከላይ ያስቀመጥኩት ችግር እንዳለ ሆኖ ሴቶች በቤተሰብ ደረጃ ከልጅነታቸው ጀምሮ በተለይ በታዳጊነት እድሜያቸው በሰውነታቸው ፤በስሜታቸው እና በአስተሳሰባቸው ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሲመጣ ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ ጋር በቅርበትና በግልፅነት ለውጦችን እንዴት መቀበል እንዳለባቸው ስለማይወያዩ እና ግንዛቤ ስለማይሰጣቸው በዚህ ከባድ የእድሜ ክልል ላይ ለሚገጥሟቸው ጉዳዮች ሁሉ ከነሱ ጋር ተመሳሳይ በሆነ የእድሜ ክልል ላይ እና የግንዛቤ መጠን ካሉ ጓዶቻቸው ጋር ብቻ በመወያየት ጊዜያዊ ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን የሚያረካ ውሳኔ በመወሰን ወደፊት ሊሆኑ ያለሙትን ግብ ሳያዩ በአጭር ሲቀጩ የምናያቸው ሴቶች በርካታ ናቸው። ታዲያ በዙርያቸው ያለው ማህበረሰብ ደግሞ የኛ ሚና ምን ነበር ብሎ ሳይሆን የሚጠይቀው የተለመደውን አባባል አይ የሴት ነገር በማለት ተስፋ አስቆራጭ የሆነ አስተያየት ከመስጠት ውጪ አስተማሪ የሆነ ግብዓት ሲሰጥ አይታይም።

እኔ ግን አጥብቄ መከራከር የምፈልገው ምንም አንኳን ሴት በመሆንዋ ሊገጥማት የሚችትለው ነገር ብዙ ቢሆንም ከፊትዋ የሚገጥሟት መሰናክሎች መውጣት የምትችለው የራስዋ የሆነ ራዕይ እና የህይወት ተልዕኮ ሲኖራት ነው። አንድ ሴት መሆን የምትፈልገውን ነገር ዛሬ ላይ ሆና ማየት (ማለም) ከቻለች በየዕለቱ የሚገጥምዋት ነገሮች ሁሉ ወደ ፈለገችው ቦታ ለማድረስ የሚያግዙ ናቸው ወይስ እንዳትደርስ የሚያሰናክሉ ናቸው እሚለውን መለየት ያስችላታል ። Sean Covey : The Seven Habit of Highly Effective Teen በሚለው መፅሃፈቸው እንዳስቀመጡት (Proactive People) በአመክንዮ መልስ የሚሰጡ ሰዎች እለት እለት በነሱ ላይ የሚፈጠር ነገር ሁሉ መቆጣጠር እንደማይቾሉ ተገንዝበው እያንዳንዱን ሁኔታ ወይም ተግዳሮት ምን አድርግው በቁጥጥር ስራ ማዋል እንዳለባቸው ያውቃሉ ይላሉ ።

እኔም ፅሁፌን ሳገባድድ በሴትነታችን ሊገጥሙን የሚችሉ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም ራዕያችንን እውን እንዳይሆን የማድረግ ጉልበት የምንሰጣቸው አልችልም በማለት የራስን አቅም ባለማወቅና ባለማሳድግ የምንፈጥረው የአስተሳሰብ ዉስንነት ዉጤት በመሆኑ ልንታገለዉና በአሸናፊነት ልንወጣዉ ግድ ይለናል።

# MASK FOR GEDIO ZONE!









#Mask for Gedeo Zone
#በጌዴኦ ለሚገኙ 10 ሺህ ወገኖች የፊት ጭምብል (Mask) የማሰባሰብ ዘመቻ

Mask For Gedeo በሚል አቅም ለሌላቸው የገጠር ማህበረሰብ የፊት ጭምብል የማሰባሰብ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ እየተካሄደ ይገኛል። በመጀመርያው ዙር ማስክ የማሰባሰብ ዘመቻ በስድስት ቀን ውስጥ ብቻ ከ4000(አራት ሺህ) በላይ ማስኮች የተሰበሰቡ ሲሆን በወናጎ ፣ በዲላ ዙሪያ እና በኮቸሬ(ጨለለቅቱ) የማስክ እደላ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

በቀጣይ ለ6000(ስድስት ሺህ) ወገኖች የፊት ጭምብል ለማድረስ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለመስራ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛሉ።

በዚህ ስራ ላይ አብራችሁን መስራት ለምትፈልጉ የአስተባባሪዎች ስልክ
1) 0927131207-----ነፃነት ጌታቸው
2) 0916501623---ብሩክታዊት በቀለ
3) 0911991503 --ቢንያም ሽፈራው
#ቅንነት_ድል_ያደርጋል!



ዮናስ ጋ/ማርቆስ
lijyoha@Gmail.com

ሰላም! እንደምን ከረማችሁ ውድ የቅንድል ዲጅታል መፅሔት ቤተሰቦች? ዛሬም እንደ ሁል ጊዜው ብታነቧቸው ያዝናናሉ፣ ያስተምራሉ ብዬ ያሰብኳቸውን መፅሐፍት እጠቁማችኋለሁ። በዚህ የኮቪድ19 ወረርሽኝ ወቅት አስገዳጅ ሁኔታ ካልገጠማችሁ በቀር ከቤት ባለመውጣት ራሳችሁን እና ቤተሰቦቻችሁን እየጠበቃችሁ በዚህ እቤት በምታሳልፉበት ጊዜ ለራሳችሁ የንባብ ጊዜ በመስጠት እንድታሳልፉትና ወደፊትም ማንበብን የህይወት ልምድ ማድረግን እንለማመድ እላለሁ። "ማንበብ ነጻ ያወጣል" እያልኩኝ የዛሬውን የመፅሐፍ ጥቆማዎቼን እነሆ ተጋበዙልኝ።




## ምንትዋብ

ደራሲ: ህይወት ተፈራ
ገጽ ብዛት: 270
ይዘት: ታሪካዊ ልቦለድ
ዋጋ: 150 ብር





## ፍኖተ አእምሮ /የእውቀት ጎዳና/

ደራሲ፡ ልዑል ራስ ካሳ ኃይሉ
ገጽ ብዛት: 301
ይዘት: ራስ አገዝ
ዋጋ: 176.65ብር





## ሀሽማል

ደራሲ፡ ማዕበል ፈጠነ
ገጽ ብዛት: 393
ይዘት: ልቦለድ
ዋጋ:152 ብር




## ጥበብ

ደራሲ፡ ኃይለጎርጊስ ማም
ገጽ ብዛት: 576
ይዘት: ፍልስፍና
ዋጋ:200 ብር




## የቃየን መሥዋዕት

ደረሲ፡ ሰርቅ ዳ.
ገጽ ብዛት: 304
ይዘት: ልቦለድ
ዋጋ:68.50 ብር

#ትዝብት

ቀለዮጳ ደስታ
cleopadada2012@gmail.com



# አደኖችህ ወዴት ደያሉ

እ.ኤ.አ 1950 ጀምሮ የታወቀ አንድ የፖለቲካ አቋም ነበር- ማካርቲዝም የሚባል። የዚህ አስተሳሰብ ዋና አላማ ተፎካካሪ የሚሆኑ ሰዎችን በሀሳብ ታግሎ ከማሸነፍ ይልቅ ምንጫቸው ባልታወቀ ክሶች ስማቸውን ማጠልሸት እና ማዋረድ ላይ ያተኩራል። አንድን ሰው ስታዋርደው ጠንካራ አቋም የሌለው እንደሆነ፣ አልያም የተከሰሰበት ክስ እውነትነት ካለው ከውድድሩ ሜዳ መራቁ አይቀርም። ምንም እንኳን ጠንካራ ሀሳብ ያለው ቢሆንም ጠንካራ አቋም ስለሌለው ብቻ ተሸናፊ ይሆናል።

እስቲ የእኛን አኗኗር እንይ... ስንቶቻችን ነን የራሳችን የሆነ አቋም ያለን? ስንቶቻችንስ ነን የሌላውን አቋም የምናከብር? በሀሳብ፣ በድርጊት፣ በችሎታ፣ በስኬት፣ በሀብት የሚበልጠን ሰው ስናገኝ ቀድመን የምናስበው ምን ይሆን? በተቃራኒው ከእኛ በሁሉም ነገር የሚያንስ ሰው ስናገኝ እንዴት ይሆን የምናስታምመው?

የአመንዝራይቷን ታሪክ ብንጠቅስ ትልቅ መማሪያ ይሆነናል። አንዲት ሴት ነበረች፣ ስታመነዝር እጅ ከፍንጅ የተያዘች (ወንድየው መያዙን አላወቅንም)... “ በሙሴ ሕግ እንደዚህ አይነት ድርጊት ሲያደርጉ የተገኙት ይገደሉ’ ይላል፤ አንተስ ምን ትላለህ ብለው መምህሩን ጠየቁት።

“ ከእናንተ ኃጢአት የሌለባት ይውገራት” አላቸው።

ከሳሾቿም ህሊናቸው ወቅሷቸው ተበተኑ ይላል (ዮሐ 8:3-9)። ዘመናችንን እንመልከት። ሰንሰለት ድራማ የምትሰራ ተዋናይ ከወንድ ጋር ተያዘች ተብላ ሀገር ሙሉ የስድብ ናዳ ሲያወርድባት፣ እውነት ወይ ውሸት መሆኑን ሳናውቅ... አይዞሽ እንኳን ሊላት የደፈረ አንድም አልነበረ። በቅርቡ ደግሞ ሄኖክ ድንቁ የተባለው አርቲስት በተወራበት ወሬ ስሙን ከማንቋሸሽ እና ማላገጫ ከማድረግ ባለፈ ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ እንዲደረግለት ወይ በጸሎታችን እንድናስበው የነገረን ሰው የለም።

እነዚህን ሰዎች አዋረድናቸው... ላይናገሩት ይችሉ ይሆን እንጂ የተሰበሩበት ነገር አላቸው። በዚህ መካከል ግን ራሳችንን አይተን ይሆን? ንጽህናችን ምን ያህል ነው? ለመውቀስ ያበቃን ማንነታችን ምንኛ የተስተካከለ ነው? በእውነቱስ ከሆነ ንጹህ ማንነት ያለው ሰው ያዋርዳል ወይስ ለተከፋት ያዝናል? አንባቢ ሆይ ይህን እያሰላሰልክ አንድ በደርግ ጊዜ ወደተፈጸመ ታሪክ ልውሰድህ...( ትግላችን እና ነበር ከሚል መጽሐፍ የተወሰደ ነው)

ደርግ ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ስልጣን ሲረከብ ባስጠናው ጥናት ሀገሪቱ የነበራት የደን ሽፋን በ20ኛው ምዕተ-ዓመት መባቻ 60% በመቶ የነበረው የደን ክምችት ወደ 4% በመቶ አሽቆልቁሎ ነበር (ትግላችን ገጽ 60- መንግሥቱ ኃይለአርያም)። ይህን ታሳቢ በማድረግም አረንጓዴ ዘመቻ በሚል እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር። የምርት ዘመቻ ዋና እና ምክትል የነበሩት ሻምበል ታምራት ፈረደ እና ሌተናንት ኮሎኔል እንዳለ ተሰማ የግል ቅራኔ ነበራቸው። ስለ አረንጓዴ ዘመቻው ጥናት ሴሚናር ለማቅረብ (የሚቀርብበት ቦታ ፓርላማ ነው ልብ በሉት) ያዘጋጀውን የመወያያ ጽሑፍ እንዲያሳዩት ሌተናንት ኮሎኔል እንዳለ ተሰማ ሲጠይቁት... ሻምበል ታምራት ጽሑፉ እሳቸው እንዲያዩበት ስላልፈለገ አልሰጥም አላቸው። ንትርክ ውስጥ ገቡ። ከዚያን ሻምበል ታምራት ፈረደ በድፍረት ጽሑፉን ሴሚናሪው ላይ አቀረበ (ሌሎች ያቀረቡም ነበሩ)። ከሻይ እረፍት በኋላ መድረኩ ለውይይት ሲከፈት የሚሰነዘሩት ሀሳቦች በሙሉ የሻምበል ታምራት ፈረደ ጽሑፍ ላይ ብቻ ሆኑ።

ሻምበል ታምራትም ሻምበል ለገሠ ከተባሉ ከደርግ ባለስልጣን ጋር (አንባቢ ሆይ ይህንን ታሪክ ‘ነበር’ ከሚል መጽሐፍ ገጽ 355-370 ድረስ ማግኘት ትችላለህ- ዘነበ ፈለቀ እንደጻፈው) ግጭት ስለነበረው... በፓርላማ ውስጥ በተፈጠረው ንትርክ አማካይነት ሻምበል ለገሠን የሚደግፍ መቶ አለቃ ደስታ ታደሰ የተባለ የደርግ አባል ሻምበል ታምራት ላይ ውርጅብኙን አወረደባቸው። “... የአቀረበው የመወያያ ጽሑፍ ኢ-ሳይንሳዊና ቀልባሽ አስተሳሰብ የተጠናወተው፥ ጋጠወጥነትና ራስን ከፍ የማድረግ እብጠት የታየበት ነው...” የሚል ነበር።
ሻምበል ታምራት ተዋረደ... በዚያን እለትም ለሊቀመንበር መንግሥቱ የተፈጠረውን ለመናገር ሲሄድ ኮማንዶዎች ሸምቀው ጠብቀውት ኖሮ ጉዳዩን ለሊቀመንበሩ ሳይናገር አደረ። በነጋታው ንትርኩ እንዲፈታ ሊቀመንበር መንግሥቱ ሻምበል ፍቅረሥላሤን ወደፓርላማ ላኩ። ሻምበል ፍቅረሥላሤ ግን ከአቅማቸው በላይ ሆነ።
ከሰዓት በኋላ ሊቀመንበር መንግሥቱ በፓርላማ ተገኙ። የተፈጠረውን ችግርም እንዲያብራሩላቸው ጠየቁ። አቤት... አስተያየት ሰጭዎች ሻምበል ታምራት ፈረደ ላይ ያወረዱባቸው ትችት.... “ ጓድ ታምራት ትዕዛዝ ለመቀበል ፍቃደኛ አልሆነም... የሻምበል ታምራት ፈረደ ንግግር የአብዮቱን ድሎች ያኮሰሰ... እንደሻምበል ታምራት አይነት ተራና ኢሳይንሳዊ ንግግር እንድናዳምጥ ለምን እንጠራለን...” የሚሉ ነበሩ።
ጓድ ሊቀመንበርም የሻምበል ታምራት ፈረደን ንግግር (በቴፕ የተቀዳ) ካዳመጡ በኋላ “ሀገራችን በሁሉም አቅጣጫ የታፈረችና የተከበረች እንድትሆን የምናደርገውን ጥረት አትደግፉም እንዴ? ታድያ የጓድ ታምራት ንግግር ከዚህ ውጪ ምን አነሳ...” ብለው ተናገሩ።
ከዚህ በላይ የተጻፈው አነስተኛ ታሪክ ማንንም ለመተቸት እና ለመደገፍ አይደለም። ይልቁኑ እንድንማርበት እንጂ። የአንድን ሰው ንግግር፣ ሀሳብ፣ አቋም የምንመዝነው በንግግሩ፣ በሀሳቡ ብቻ ወይስ እኛ ከማንወድለት መስፈሪያ አንፃር?
መጽሐፍ እንዲህ ይላል ... አስቀድመህ በዓይንህ ያለውን ምሰሶ ሳታወጣ የባልንጀራህን ጉድፍ አትመልከት። አንዳንዶቻችን ከመቃብር የበለጠ አስፈሪ ማንነት ኖሮን ነው ሰውን ምናዋርደው... ስልክ እንጨት የሚያህል ቆሻሻ በዓይናችን ሞልቶ ነው አንዲት ብናኝ አፈር ከሌላው ለማውጣት ምንሮጠው...
ታድያ አንባቢ ሆይ ዓይኖችህ ወዴት ናቸው? ወደራስህ? ወደውድቀትህ? ወይስ ወደሌላው? ወደችግራቸው? የጠቢባን ዓይኖች በራሱ ላይ ናቸው እንዲል መጽሐፉ ጠቢብ ሁን፣ ዓይኖችህን ወደራስህ መልስ... ሌላውን ደግሞ በድካሙ ጊዜ ከምታዋርደው ይልቅ ደግፈው፣ አጽናናው፣ ከጎኑ ሁን....
ያ ነው ጥበብ!
ቸር ያገናኘን።

# ኢትዮጲያ በዩኔስኮ የዓለም ቅርስ አድርጎ ስላስመዘገበቻቸው ቅርሶች ምን ያህል ያውቃሉ?

የኮንሶ ተራሮች ሰው ሰራሽ እንከን - ሀምሳ አምስት ካሬ ኪ.ሜ ስፋት ያለው የኮንሶ ተራሮች ሰው ሰራሽ እርከን እና የኮንሶ ባህላዊ ቅርስ በ2011 ዓም በዩኔስኮ የአለም ዝርዝር ውስጥ ተካተተ።

ላሊበላ- በአስራ ሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በንጉሥ ላሊበላ የታነፁት አብያተክርስቲያናት በ1978 ዓም በዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ተብለው ተካተዋል።

የፋሲል ግንብ- በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት በጎንደር ከተማ ማዕከል ባለ ከፍታ ስፍራ ላይ የፋሲል ግንብ በ1979 ዓም በዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ተብሎ ተመዝግቧል።

ጥያ ትክል ድንጋይ- ሶዶ ውስጥ የሚገኘው ይህ ትክል ድንጋይ የአለም ቅርስ ተብሎ በ1980ዓም ተመዝግቧል።

ጀጎል ግንብ - በዓለም አራተኛው የእስልምና ቅዱስ ከተማ የሆነውና በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተገነባ የሚነገርለት የሀረር ግንብ (ጀጎል) በ2006ዓም ሌላው የአለም ቅርስ ተደርጎ የተመዘገበ ነው።

የሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ- በአማራ ክልላዊ መንግስት ከጎንደር ከተማ በ120 ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኘው የሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ በ1978 ዓም የዓለም ቅርሶች ዝርዝር እንደ አንዱ ሆኖ ተመዘገበ።


የአክሱም ሀውልት- በአክሱም ከተማ የሚገኙት ሀውልቶች፣ የአለት ጥርቦች ፣ የነገስታት መካነ መቃብሮች ከአንደኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ጀምሮ እስከ አስራሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በተለያዩ ጊዜ የታነፁ እና የተገነቡ ድንቅ የስነ ህንፃ እና ስነ ቅርፅ ውጤቶች ሲሆኑ 1980 ዓም በዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ተብለው ተመዝግበዋል።

አዋሽ ሸለቆ- የጥንታዊ የሰው ዘር መገኛ ምንጭ የሆነው የአዋሽ ያታችኛው ሸለቆ በ1980ዓም የዓለም ቅርሶች ዝርዝር ውስጥ ተመዘገበ።

ኦሞ ሸለቆ- የጥንታዊ ሰዎች ቅሪተ አካል የተገኘበት የኦሞ ታችኛው ስምጥ ሸለቆ በ1980 ዓም ስድስተኛው በዩኔስኮ የተመዘገበ የአገራችን ተፈጥሮአዊ ቅርስ ነው።

#ሳይ ቴክ

ለዓለም ክንፈ
lexkinfe5@gmail.com



# በቀጣዮቹ አስርት ዓመታት ሰርጓጅ መርከቦች ባዕዳን ውቅያንኖሶችን ሊቃኙ ነው።

በቅርቡ በስፔስ ዶት ኮም የወጣው ዘገባ በቀጣዮቹ አሥርት ዓመታት ሰርጓጅ መርከቦች የሳተርን ጨረቃ ውቅያኖሶች ይቃኛሉ ነው የተባለው። በዚህ ግዙፍ የፀሐይ ስራዓት በስድስተኛ ቦታ ላይ በቀለበቶቿ አሸብርቃ የምትገኘው ሳተርን፤ ብዙ ጨረቃዎች አሏት። ከእነዚህም መካከል ከመልከዓ ምድሯ ስር ትልቅ ውቂያኖስን የያዘችው ታይተን የተባለችው የሳተርን ጨረቃ በግንባር ቀደምትነት ስትጠቀስ በህዋ ላይ የሥነ ህይወት ተመራማሪዎችን ቀልብ ወስዳለች። ሰሞኑን ታዲያ ተመራማሪዎቹ  ይቺህ ከሳተርን ጨረቃዎች በግዝፈት ሁለተኛ ደረጃ ላይ የምትገኘው ጨረቃ ጋር ሰርጓጅ መርከብን ልከው ስነ ምህዳሯን ለማጥናት ያቀዱ ይመስላል። ይህ የሰርጓጅ መርከብ ተልዕኮ የታይታንን ሃይድሮካርቦናዊ ሐይቆች እና ውቂያኖሶች እንደሚያጠና ይጠበቃል።

ይህ ተልዕኮ በናሳ ከፀደቀ በ2030ዎቹ ወደ መዳረሻው እንደሚላክ ይጠበቃል። “እኛ እንደምናምነው ወደ ታይታን የሚላከው ይሄ ሰርጓጅ መርከብ በዓይነቱ የመጀመሪያው ከመሆኑ በተጨማሪ በቀጣይ ወደ ዩሮፓ እና ኢንሴላደየስ ለሚላኩ ተመሳሳይ ተልዕኮዎች እንደ ተሞክሮ ይጠቅመናል” ሲል የናሳው ግሌን ምርምር ማዕከል ሰራተኛ ስቲቭ ዖሊሰን ተናግሯል። ዩሮፓ እና ኢንሰላዲየስ የጁፒተር እና የሳተርን ትላልቅ ጨረቃዎች ሲሆኑ ሁለቱም ግዙፍ የፈሳሽ ውሃን ውቂያኖስ ይይዛሉ። ነገር ግን ውቂያኖሶቻቸው በወፋፍራም የበረዶ ቅርፊቶች በጥልቁ ውስጥ የተቀበሩ ስለሆኑ ለቀጣይ የሰርጓጅ መርከብ ተልዕኮዎች እንደ ታይታን አመቺ አይሆኑም ተብሎ ይጠበቃል።

ግር የሚያሰኝ እና ምናልባትም ሕይወትን መደገፍ የሚችል ዓለም ይሆን?

በ5150 ኪሎ ሜትር ስፋት ታይታን ከጁፒተሩ ጋሚኒድ ቀጥሎ በስርዓተ ፀሐያችን ውስጥ ሁለተኛው ትልቁ ጨረቃ ነው። ነገር ግን ታይታንን ልዩ የሚያደርገው ግዝፈቱ ብቻ ሳይሆን ከምንኖርባት መሬት ውጪ ፈሳሽ አካላትን የያዘ የተረጋጋ መልከዓምድራዊ አቀማመጥ በመያዙ ነው። እነዚህ የሚቴን እና ኢቴን ባህሮች ከሰሜን አሜሪካዎቹ ታላላቅ ሐይቆች እንደሚልቁ ይነገራል። በተጨማሪም የታይታን እንደ አባበሮ ወፍራም የሆነ ከባቢ አየር ውስብስብ የሆነ የኦርጋኒክ ሞለኪዩሎችን እና ለህይወት አስፈላጊ የሆነውን ካርቦን ጨምሮ ጠቃሚ ግብዓቶችን ይዟል።

በዚህም ምክኒያት ይመስላል አስትሮባየሎጂስቶች ታይታን ምናልባት ህይወት ያላቸው ፍጡራን ቢኖሩባት እንኳን የሚኖሩት በዛ ወፍራም ከባቢ አየሯ ላይ እየተንሳፈፉ ወይንም ከመልከዓምድሯ ስር ባሉት ውቂያኖሶቿ እየዋኙ እንደሆነ የሚያስረዱት። እነዚህ ፍጡራን ምድራችን ላይ ካሉ ፍጡራን በፍፁም የሚለዩ እንደሆኑ የሚናገሩት ሳይንቲስቶቹ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ታይታን ባላት ጨዋማ ባህር እና በመልከዓምድሯ ላይ በህይወት ለመቆየት በጣም ቀዝቃዛ በመሆኗ ነው በማለት መላምታቸውን ያስቀምጣሉ።

የሃይድሮ ካርቦኖቹን ባህሮች ማሰሱስ እንዴት ሊካሄድ ነው?

እስካሁን ስለ ታይታን ያለን ዕውቀት ወደ ላቀ ደረጃ የተሸጋገረው ካሲኒ ሃይገንስ ተልዕኮ በተባለው የባለ 3.2 ቢሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ነው፣ ይህ ፕሮጀክት ሳተርንን እና ጨረቃዎቹን እ.ኤ.አ ከ 2004 እስከ 2017 ድረስ ሲያጠና የቆየ ሲሆን፤ የናሳው ካሲኒ ኦርቢተር እና በአውሮጳ እና ጣሊያን ስፔስ ኤጀንሲዎች በ2005 የተላከው ሃይገንስ ላንደር ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። ናሳ ባሁኑ ወቅት ድራጎን ፍላይ የተሰኘውን የራሱን በባለ ስምንት ክንፍ ሰው አልባ መንኮራኩር እየሰራ ሲሆን እ.ኤ.አ በ2026 ላይ ወደ ታይታን ይላካል ተብሎ ይጠበቃል። ነገሮች እንደ ታቀዱት ከሄዱ ደግሞ በ2034 ድራጎን ፍላይ ታይታን ላይ ሲያርፍ የጨረቃዋን ውስብስብ ኬሚስትሪ እና ህይወት ሊኖርበት የሚችልባቸውን ቦታዎች ይለያል ተብሎ ይጠበቃል።

ከዚህ በኋላ ነው እንግዲህ ሰርጓጅ መርከቦቹ ቀጣዩን ጥናት ለማድረግ ወደ ታይታን የሚላኩት። ናሳ እንካሁን በይፋዊነት ይሄንን ተልዕኮ ባያፀድቀውም ኦሊሰን እና ቢድኑ ግን ጥናታቸውን እንዲቀጥሉ በማሰብ በ 2014 እና 2015 ላይ በድምሩ የ600,000 ዶላር በጀት ተለቆላቸው ነበር። “ይህ ድጋፍ በNIAC የተሰጠ ሲሆን ዋናው አላማውም መሰረታዊ የሆኑ የምህንድስና ዕቅዶችን ለታይታኑ ሰርጓጅ መርከብ ማዘጋጀት ነበር። “ ነገር ግን” የቡድኑ መሪ ዖሊሰን ቀጠለ “ ነገር ግን ይህንን እንዴት ማካሄድ እንችላለን? ምን አይነት ቴክኖሎጂያዊ ውጤቶች ያስፈልጉናል? ስለ ታይታን መልከዓምድር ምን እናውቃለን?” በማለት ነበር ጥያቄዎቹን በFISO ፕረዘንቴሽን ላይ የገለፀው። ምላሾቹም ግልፅ ነበሩ። የታይታን ልዩነት ወጣ ያለ ነው። ለምሳሌ ታይታን ለጨረቃነት ትልቅ ብትሆንም ከመሬት አንፃር ግን በመጠን ታንሳለች። ከዚህ በተጨማሪም የመሬትን 14 በመቶ ብቻ የሆነ ስበትን ስትተገብር ይህ ማለት አሁን መሬት ላይ ያሉት ሰርጓጅ መርከቦች ባህሮች ውስጥ በታወቀ የጥልቀት መጠን ከሚያጋጥማቸው የግፊት መጠን በጣም የቀነሰ ግፊት ታይታን ላይ ቢሄዱ ያገኛሉ።
ይህም በጥልቀት ውቂያኖሶቿን ለማሰስ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም እንደ ዖሊሰን ገለፃ ሰርጓጅ መርከቦች ከውሃ በተሻለ ሁኔታ በሃይድሮካርቦን ፈሳሾች ውስጥ በነፃነት የመጓዝ ዕድላቸው ይጨምራል። በሚያስደንቅ ሁኔታም የታይታ ሃይድሮካርቦናዊ ውቂያኖሶች ራዲዮ ትራንስፓረንት ወይንም የራዲዎ ሞገድን ሙሉ በሙሉ የሚያሳልፉ በመሆናቸው መሬት ላይ ካለ የመቀበያ ጣቢያ ጋር የተሻለ ሞገዳዊ ግንኙነትን መፍጠር ይቻላል።
ታዲያ ይህ ሰርጓጅ መርከብ ምን ያህል ይመዝን ይሆን?
ሰርጓጅ መርከቡ በራሱ ትልቅ መሆን አለበት። ይህም ግዝፈት  ወደ 6 ሜትር ርዝመት እና 1,500 ኪሎ ግራም መጠነ ቁስን ሲመዝን የግንኙነት እቃዎችን ጨምሮ  የተለያዩ ለተልዕኮው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በአግባቡ ለመያዝ  ነው ሲል ዖሊሰን ይገልፃል። ጥልቅ ሰርጓጁ ከዖርቢተሩ ጋር በአንጻሩ ደግሞ ተመሳሳይ የሳይሳዊ ዕቃዎችን ለመያዝ 2ሜትር ርዝመት እና 500 ኪሎግራምን ሊይዝ ይችላል።
ይህ የሳይንሳዊ ዕቃዎች ስብስብ ማካተት ካለባቸው ግብዓቶች መሃከል የፈሳሽ ናሙናዎቹን ለማጥናት የሚያገለግል የኬሚስትሪ ቁስን፣ የመልከዓምድር ቃኚ ካሜራን፣ ድምፃዊ የጥልቀት መለኪያን፣ የአየር ሁኔታ ጣቢያን እንዲሁም በአካባቢው ያሉትን ተፈጥሯዊ ቁሶች አፈጣጠር የሚያጠና መሣሪያን መያዝ ያስፈልገዋል ሲሉ ዖሊሰን እና ቡድኑ ይገልፃሉ።  ሁሉም ወደ ታይታን የሚላኩ ሰርጓጆች በኒውክሊየር እንደሚሰሩ ሲገለፅ፤ ይህም የሆነበት ሳተርን ለፀሐይ የመሬትን 10 እጥፍ ርቃ በመገኘቷ ከፀሐይ ብርሃን የሚገኘው ብርሃን በጣም ደካማ በመሆኑ ነው።
ታዲያ በ2030 ምጥቂያው ይከናወናል?

የታይታን ሰሜናዊው ንፍቀ ክበብ ሁለቱን ለተልዕኮው ምቹ ይሆናሉ የተባሉትን ባህሮች ይዟል። የመጀመሪያው ክራክን የተባለው 400 ሺህ ስኩየር ኪሎሜትርን ሲሸፍን ወደ 35 ሜትር ጥልቀት አለው። ሁለተኛው ሊጌያ የተባለው ባህር ደሞ 50 ሺህ ስኩየር ኪሎሜትርን ሲያካልል ወደ 170 ሜትር ጥልቀት አለው። ታዲያ ልክ እንደ ሳተርን ሁሉ ታይታንም እያንዳንዱ ወቅቶቿ 7 የመሬት አመታትን በሚያህል ቆይታ ይፈራረቃሉ። “የታይታን ሰሜናዊ ንፍቀ ክበብም በበጋው ወቅት ሰርጓጆቹ ቢላኩ እና በ2045 ቢደርሱ ከምድር ጋር ካለ መቆጣጠቂያ ጣቢያ ጋር ለመገናኘት አመቺ ይሆናል”። “አልያም” ብሎ ይቀጥላል ሆሊሰን፤ “አልያም በጸደይ ወቅት ማለትም በ2040 ሰርጓጁ ከአጋዥ ኦርቢተር ጋር ታይተን ጋር ቢደርስ ተመሳሳይ የሆነ መረጃን ማግኘት ያስችለናል። “
ወደ ታይታን ለመድረስ ድፍን 7 ዓመታት ይፈጃል። በመሆኑም ሰርጓጆቹ በናሳ ፀድቀው ቢላኩ እንኳን የግድ በ2030ዎቹ መሆን አለበት። ይህ ካልሆነ ግን ተመሣሣይ ብርሃናማ ወቅትን በታይተን ላይ ለማግኘት እንደገና ሦሥትዐሥርትዓመታትን መጠበቅ ሊያስፈልገን ይችላል ሲል ሆሊሰን ጥናቱን ይቋጫል።
ምንጭ ፦ space.com
https://www.space.com /saturn-m oon-titan-subm arine-concept-m ission.htm l































# ቅንድል መፅሔት

TELEGRAM :- @KENDELM

FACEBOOK :- @KDIGITALMAGAZINE